# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 198 መጋቢት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# የድርቅ ስጋት ባለባቸው አካባቢዎች

## ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ኢንቨስትመንት ሊኖር ይገባል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ተደጋጋሚ ድርቅና የአየር ንብረት ለውጥ በሚያጋጥምባቸው አካባቢዎች ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ኢንቨስትመንት እንደሚያስፈልግ ምሁራን ተናገሩ። ድርቅ ባጋጠማቸው አካባቢዎች እየተደረገ ያለው ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም አሳስበዋል።

የተፈጥሮ ሀብትና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሙያ ዶክተር ተሻለ ወልደአማኑኤል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የተፈጥሮ ሀብቱ በከፍተኛ ደረጃ እየተመናመነ በመምጣቱ ተደጋጋሚ የተፈጥሮ አደጋዎች በኢትዮጵያ እየተከሰቱ ነው። ይህንንም ለመከላከል ውጤታማ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና አጠቃቀም ያስፈልጋል።

ድርቅንና የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም


የድርቅ ስጋት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## በባህርዳር በ743 ሚሊዮን ብር የውሃ ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ ነው

- በቀጣይ ሁለት ወራት አገልግሎት መስጠት ይጀምራሉ


ገጽ 4


## የብዝሀ ሕይወት ሀብት

ከምርምር ባለፈ ለገበያ እንዲውል አልተደረገም


ገጽ 4


# ሰው መሆንን

## በተግባር ያሳዩ ወጣት

**ዳግማዊት ግርማ**

ሰው ጠፋ፤ መልካምነት ራቀ፤ በትውልዱ ክፋት ነገሰ፣ ራስን መውደድ ተመለከ፤ ወዘተ የሚሉ ሃሳቦች በዚህ ዘመን በተደጋጋሚ የምንሰማቸው ሃሳቦች ናቸው። በዚህ መሀል ግን የቸርነትና የደግነት እንዲሁም ሰው የመሆን ጥግንም አይተናል። «ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው» ብሎ የተነሳውን የዘመናችንን የደግነት ተምሳሌት ድርጅት በሁለት እግሩ ለማቆም ሌሎች ደጋጎች ከጎኑ ተሰለፉ።

ራስንና ወጣትነቱን ያሸነፈ ትውልድ መጣ፤ የዚህ ትውልድ ቅኖች ዘመኑን ሊዋጁ ተገኙ። ባለ ደግ ልቦች ባልተዋለላቸው ውለታ፣ ውለታ ከፋይ ሆኑ። የየትውልዱን ዕዳ በመልካም እጆቻቸው አፍሰው መለሱ። የበጎነት ሰንደቅ የጥሩ መሆን አርማ ሆኑ። ከነዚህ መሀል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመልካም ተግባሩ የብዙዎችን ቀልብ የገዛው የበጎነት ተምሳሌቱ ቢንያም በለጠ ተጠቃሽ ነው።

የክቡር ዶክተር ቢንያም በለጠ ነገር ብዙ ተብሎለታል። የተባለውም ያልተባለውም መልካም ቃል ያልገለፀው የክፍለ ዘመኑ ባለ ቅን ልብ ነው። ሰዎች እሱን ለመግለፅ ሊሉት ሽተው አፋቸው ባልታዘዘላቸው ቃላት


ሰው መሆንን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




የክቡር ዶክተር ቢንያም በለጠ



ኮሜዲያን እሸቴ መሰሰ
















# በአዲስ አበባ ከ2 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሀብቶች ወደ ሥራ ገብተዋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ባለፉት 8 ወራት ከ2 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሀብቶች ወደ ሥራ መግባታቸውን የከተማዋ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ግርማ ሰይፉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በስምንት ወራት ወደ ሥራ የሚገቡ ባለሀብቶች 4 ነጥብ 38 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘግባሉ ተብሎ የታቀደ ቢሆንም በአፈጻጸሙ 2 ነጥብ 664 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሀብቶች ወደ ሥራ ገብተዋል።

ኮሚሽኑ ከዚህ ቀደም የነበሩትን የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ በተያዘው ዓመት 2ሺህ 532 አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃዶችን ለመስጠት አቅዶ እየሠራ እንደሆነ የገለጹት አቶ ግርማ በስምንት ወራት ውስጥ ለ1ሺህ 979 ባለሀብቶች አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በመስጠት የዕቅዱን 78ነጥብ1 ከመቶ ማከናወን መቻሉን ጠቁመዋል። ከዚህም ባሻገር 141 የኢንቨስትመንቶች የማስፋፊያ ፍቃድ መሰጠቱንም ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ለማውጣት የሚመጡ ሁሉንም ተገልጋዮች ያለምንም መጉላላት እንዲስተናገዱ እያደረገ እንደሆነ ገልጸው ለተገልጋዮች ተገቢውን ክብር መስጠት በኮሚሽኑ ትኩረት የተሰጠው ተግባር እንደሆነ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ግርማ ገለጻ፤ ኮሚሽኑ ከዚህ ቀደም ከነበረው በበለጠ ወደ ባለ ሀብቶቹ በመቅረብ ፍቃድ የወሰዱ ባለሀብቶች ቶሎ ወደ ሥራ እንዲገቡ የክትትል እና የድጋፍ ሥራዎችን በመሥራት እና ችግሮቻቸውን በመፍታት ጠንክሮ እየሰራ ነው። ከተለያዩ የአገልግሎት ክፍያዎችም በስምንት ወራት ውስጥ 18 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ 17 ነጥብ 4 ሚሊዮን ብር በመሰብሰብ የዕቅዱን 95 ነጥብ 6 በመቶ ማሳካት ችሏል።

ኮሚሽኑ በተያዘው ዓመት ወደ ሥራ የሚገቡ ባለሀብቶች ለ5 ሺ ሰዎች ቋሚ እና ጊዜያዊ የሥራ ዕድሎችን እንደሚፈጥሩ ያቀደ ቢሆንም ወደ ሥራ የገቡ ኢንቨስትመንቶች የፈጠሩት የሥራ ዕድል ከታቀደው በላይ እንደሆነ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ግርማ አገላለጽ ወደ ሥራ የሚገቡ ባለሀብቶች አዲስ አበባ ውስጥ የመስሪያ ቦታ እንዲቀርብላቸው የሚጠይቁ ቢሆንም በሚፈለገው መጠን የመስሪያ ቦታ ማዘጋጀት አልተቻለም። ይህ ደግሞ ከኢንቨስትመንት ጋር ተያይዞ የሚገጥም ችግር ነው።

በመዲናዋ በኢንቨስትመንት የሚሰማሩ ባለሀብቶች ቀደም ሲል ቦታ ከወሰዱ ሰዎች እና የግለሰቦችን ቤት በመከራየት ጭምር ሥራ እንደሚሠሩ የጠቆሙት አቶ ግርማ በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥም ቢሆን ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች በመዲናዋ ኢንቨስት ለማድረግ ከፍተኛ ፍላጎት እንደሚያሳዩ ተናግረዋል።



# በክልሉ በመጪው ክረምት ከ50 ሚሊዮን በላይ ችግኞች እንደሚተከሉ ተገለጸ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመጪው የክረምት ወቅት ከ50 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ዝግጅት በመደረግ ላይ እንደሚገኝ የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ባበክር ኸሊፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በክልሉ ችግኞችን የማፍላት እንቅስቃሴ በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል። በመጪው የክረምት ወቅት ከ50 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ዝግጅት በመደረግ ላይ ይገኛል።

ከባለፈው የክረምት ጊዜ ጀምሮ የችግኝ ዘር ግዢ ተፈፅሞ ሥራዎች በስፋት እየተከናወኑ ሲሆን በዋናነትም ትኩረት የተደረገው በአትክልትና ፍራፍሬ ላይ እንደሆነም አቶ ባበክር ገልጸዋል። በዘንድሮው ክረምት የሚተከሉት ችግኞች በአብዛኛው ፍሬያቸው ለምግብነት ሊውሉ የሚችሉ ናቸው ያሉት አቶ ባበክር፤ እንደ ቡና፣ ፓፓያ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ዘይቱን፣ ማንጎ አቮካዶና የመሳሰሉ ተክሎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው ብለዋል።

እንደ አቶ ባበክር ገለፃ ከፍራፍሬ በተጨማሪም ለአግሮ ፕሮሰሲንግ የሚጠቅሙ እንደ ባህርዛፍ፣ አቼኬ፣ ግራቪሊና ቀርከሀን የመሳሰሉ ችግኞችም ይተከላሉ። የሚተከሉ ችግኞች ለደን ልማት፣ ለአፈርና ውሃ ጥበቃ ጠቀሜታቸው የጎላ ነው።

ባለፉት ጊዜያት የተተከሉ ችግኞች ከዚህ በፊት በክልሉ የሚስተዋለውን የመሬት መሸርሸር መቀነስ እንደተቻለ ጠቁመው፤ በመጪው ክረምትም በተራቆቱ የክልሉ ስፍራዎች ላይ ከአካባቢው አየር ንብረት ጋር ተስማሚ የሆኑ ችግኞችን በኩታ ገጠም በመትከል የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አቶ ባበክር ገልጸዋል።

ኃላፊው አክለውም ቀደም ብለው በተተከሉ ችግኞች ምክንያት በማይታመን መልኩ አካባቢዎቹ ለም በመሆናቸው ሳር በቅሎ ለከብቶች መኖ በመሆን እያገለገለ ነው፤ የመሬት ለምነት ተመልሶ ውሃ በመፍለቁ ለመስኖነት በማገልገል ላይ ይገኛል፤ በደን ውስጥ ንብ የማነብ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው፤ እንዲሁም ከዚህ በፊት የተተከሉ ቀርከሀዎች በመድረሳቸው ለቤት ሥራና ለተለያዩ ግልጋሎቶች እየዋለ ነው ብለዋል።

ከዚህ በፊት የተሠሩ ሥራዎች ውጤታማ በመሆናቸውና ችግኝ መትከል ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን በመረዳት የኅብረተሰቡ ተሳትፎ የሚበረታታ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከ250ሺህ እስከ 300ሺህ ዜጎች የክልሉ መንግሥት ጥሪዎችን በሚያደርግበት ወቅት በነቂስ እንደሚሳተፉ አቶ ባበክር ገልጸዋል።

ባለፈው ዓመት የተተከሉት ችግኞች የጽድቀት መጠናቸው ሲገመገም የተሻለ መሆኑን የተናገሩት አቶ ባበክር፤ የተተከሉት ችግኞች በአብዛኛው መጽደቃቸውን ጠቁመው፤ ከችግኝ ዝግጅቱ በተጨማሪም በክልሉ ሌሎች የተፋሰስ ልማት ሥራዎችም በጥሩ ሁኔታ እየተካሄዱ ነው ሲሉ ጠቁመዋል።

በዘንድሮው ክረምት ለተከላ ከተዘጋጁ ችግኞች አብዛኞቹ ለምግብነት ሊውሉ የሚችሉ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን የሚያስገኙ ናቸው። በክልሉ በአረንጓዴ አሻራ የተያዘውን ዕቅድ ለማሳካት ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ችግኞችን በመትከል እና በመንከባከብ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ሊወጡ ይገባል ሲሉም አቶ ባበክር ጥሪ አቅርበዋል።

# የኦሮሚያ ባህላዊ ፍርድ ቤት ከ117ሺህ በላይ ለሚሆኑ መዝገቦች ውሳኔ ሰጥቷል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት ለኦሮሚያ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ከቀረቡት 152ሺህ መዝገቦች ውስጥ ከ117 ሺህ በላይ መዝገቦች ውሳኔ መሰጠቱን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስታወቀ።

በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ፈየራ ኃይሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የኦሮሞ ሕዝብ ሁሉንም ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉት በርካታ ባህሎችና እሴቶች ቢኖሩትም በተለያዩ ምክንያቶች ተዘንግተው መጥተዋል። በአሁኑ ጊዜም የአገሪቱን ሕገ መንግሥት መሠረት በማድረግ ባህላዊ ፍርድ ቤት ተቋቁሞ ሥራውን በአግባቡ እያከናወነ ይገኛል። በዚህም ለክልሉ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ከቀረቡት 152 ሺህ መዝገቦች ውስጥ ለ117 ሺህ በላይ መዝገቦች ውሳኔ ሰጥቷል።

ባህላዊ ፍርድ ቤት የሀሰት ምስክርነት እንዳይሰጡ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ኅብረተሰቡ ብዙ ጉዳዮችን ወደ ባህላዊ ፍርድ ቤት በመውሰዱ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት የሚመጡት ጉዳዮች በአምስት በመቶ መቀነሱንም ነው የገለጹት። በዚህም ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ለኦሮሚያ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ከቀረቡት 152ሺህ መዝገቦች ውስጥ ለ117 ሺህ 202 መዝገቦች ውሳኔ መስጠት እንደተቻለ አስታውቀዋል።



አቶ ፈየራ ኃይሉ

ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ የባህል ፍርድ ቤቱ ጉዳያቸው ውሳኔ በተላለፈባቸው ሰዎች ላይ ጥላቻን፣ ጠላትነትንና በቀልን እንዲሻር በማድረግ የሕዝቡን ወንድማማችነትና ወዳጅነት የማጠናከር ባህሪን የተለባሰ ነው።

በአንዳንድ ወገኖች በኩል ጣልቃ ገብነት መኖሩ በባህላዊ ፍርድ ቤቱ ካጋጠሙት መሰናክሎች አንዱ እንደሆነም አቶ ፈየራ ጠቁመዋል።

ከዚህም ባሻገር አልፎ አልፎ በአንዳንድ ወረዳዎች በባህላዊ ፍርድ ቤቶች ስር የተካተቱ የአገር ሽማግሌዎች የሕዝብን ጉዳይ የሚመለከቱበት ቦታ ስለሌላቸው በየደረጃው ካሉ የመንግሥት አካላት በሚጠበቀው ልክ ድጋፍ እያገኙ አይደለም ብለዋል።

ፍርድ ቤቱ በተለይ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች በፍትህ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ፈተና የሆነውን ሀሰተኛ ምስክርነት ለመቀነስ፤ በዋናነት የክልሉ ሕዝብ የቀደመ ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ ሂደትን ተከትሎ የሚያጋጥሙ አለመግባባቶችን ለመፍታት፤ የፍትህ ተዳራሽነትን የበለጠ ለማጠናከር እና የክልሉ ነዋሪዎች ፍትህ ለማግኘት ረጅም ጉዞ በማድረግ ለአላስፈላጊ ወጪ እንዳይዳረጉ ጨፌ ኦሮሚያ በክልሉ የፍትህ ተደራሽነትና ትክክለኝነትን ለማረጋገጥ ያግዛል ላለው የባህላዊ ፍርድ ቤቶች ምስረታ እውቅና የሚሰጥ አዋጅ በ2013ዓ.ም ማጽደቁ ይታወቃል።



## «ሕዝበ ሙስሊሙ የተፈናቀሉና የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳት ፆሙን ማሳለፍ ይገባዋል»

- ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የረመዳን ወር ሕዝበ ሙስሊሙ ርህራሄን የሚማርበት በመሆኑ በአገሪቱ በተለያዩ ችግሮች የተፈናቀሉ እና የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳት ፆሙን ማሳለፍ እንደሚገባው ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ ገለጹ።

ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ የ1444ኛውን የረመዳን ፆም በማስመልከት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የረመዳን ወር ሕዝበ ሙስሊሙ ከሌሎች ወራት በተለየ ሁኔታ ርህራሄን የሚማርበት በመሆኑ በአገሪቱ በተለያዩ ችግሮች የተፈናቀሉ እና የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳት ፆሙን ማሳለፍ ይገባዋል።

ረመዳን ፆም እርዳታ ለሚፈልጉ ማህበረሰቦች ከወትሮው በተለየ ሁኔታ የሚረዱበት ወር መሆኑን የገለጹት ፕሮፌሰሩ፤ የረመዳን ፆም በሕዝበ ሙስሊሙ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው በመሆኑ ከወትሮ በበለጠ እርስ በእርስ እንዲሁም ከሌሎች ወገኖች ጋር የምንረዳዳበት፣ ይቅር የምንባባልበት እና አቅመ ደካማ ወገኖችን የምንረዳበት ወር መሆኑን አስረድተዋል።

የረመዳን ፆም የሕይወት ጣዕሞች ሁሉ የሚተውበት ወር እና ሕዝበ ሙስሊሙ ከእራሱ ጋር የሚታረቅበት እንዲሁም ከፈጣሪው ጋር መገናኛ ድልድይ ነውም ሲሉም አክለዋል።

ሁልጊዜ በልተው ጠግበው የሚኖሩ ሰዎች በረመዳን ፆም በተወሰነ መልኩ ርሀብን የሚረዱበት ወር መሆኑን የገለጹት ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ፤ በመሆኑም የተራቡ ሰዎችን ማሰብ እና መርዳት እንደሚገባ ገልጸዋል።


በረመዳን ፆም ለሕዝበ ሙስሊሙም ሆነ ለአገር በርካታ ጥቅሞችን የሚያስገኝ እንደሆነ የተናገሩት ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ፣ በረመዳን ፆም የሚገኙትን የባህሪ ለውጦች በርካታ ሕዝበ ሙስሊም ቋሚ አድርገው የሚቀጥሉበት በመሆኑ የመረዳዳት እና መተጋገዝን ያጠናክራል ሲሉ አብራርተዋል።

እስልምና ሃይማኖት ተደጋገፉ እና ተረዳዱ የሚል ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ፤ እርስ በእርሳችን መረዳዳት እና መተጋገዝ ካልቻልን ሙሉ ሰው መሆን አንችልም ሲሉ አስረድተዋል።

ሕዝበ ሙስሊሙ ረመዳንን ሲፆም የተደነገገለትን ሕግ አክብሮ፤ የተቸገረውን በማብላት፣ የታረዘውን በማልበስ እና ፈጣሪን በመፍራት ሃይማኖቱ የሚፈቅደውን በማድረግ ሊሆን እንደሚገባ አሳስበዋል።

# በኢትዮጵያ ከሚመረተው ኤሌክትሪክ ኃይል አብዛኛው ጥቅም ላይ እየዋለ አይደለም

**መስከረም ሰይፉ**



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የሚመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል እና ኃይሉን ተደራሽ ለማድረግ የሚሠራው መሠረተ ልማት ዝርጋታ ሚዛኑን የጠበቀ አለመሆኑን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ ኢትዮጵያ በርካታ የኃይል ማመንጫዎችን ብትገነባም በዚሁ ልክ የሚመነጨውን ኃይል መሸከም የሚችልና ወደ እያንዳንዱ ደንበኛ የሚያደርስ መሠረተ ልማት አለመዘርጋቱን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል በአሁኑ ጊዜ የማመንጨት አቅሙ ከ5 ሺህ 200 ሜጋ ዋት በላይ የደረሰ ቢሆንም አገሪቱ አሁን ላይ እየተጠቀመች ያለው የኃይል አቅርቦት ከአንድ ሺህ 700 ሜጋ ዋት የዘለለ አለመሆኑን ተናግረዋል።

አቶ መላኩ ለዚህም ችግር መንስኤው ኃይል ለማመንጨት የሚሰጠውን ትኩረት ያህል ኃይልን ተደራሽ ለማድረግ የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ በመሆኑ ነው ብለዋል። የኃይል አቅርቦቱና ተደራሽነቱ ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ ግንባታቸው ጎን ጎን አለመካሄዱ ኢትዮጵያ የምታመነጨውን ኤሌክትሪክ ኃይል እንዳትጠቀም አድርጓታል ነው ያሉት።

የኤሌክትሪክ አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ ሌላኛው የሚያጋጥመው ችግር የኃይል ማመንጫዎች እና የተጠቃሚዎች መራራቅ መሆኑን አመልክተዋል።

እንደ አቶ መላኩ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በቂ ኃይል እያመነጨ ቢሆንም የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያዎች ቁጥር ግንባታ አነስተኛ በመሆኑ ተደራሽነቱ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል።

ከዋናው ኃይል ማመንጫ እርቀው የሚገኙ አካባቢዎችን የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽ ለማድረግ ኢትዮጵያ ካላት መልክአምድር አንጻር ጊዜ የሚፈጅ ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ ይህንን ታሳቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እርቀው የሚገኙ አካባቢዎችን ተደራሽ ለማድረግ የፀሐይ የኃይል ምንጭን እንደአማራጭ እየተጠቀመ መሆኑን ገልጸዋል። በዚህም 12 የገጠር ከተሞች በስምንት ነጥብ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የፀሐይ ኃይል ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን አቶ መላኩ ጠቅሰዋል።

አቶ መላኩ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከኃይል ተደራሽነት በተጨማሪ የኃይል መቆራረጥ ችግርን ለመፍታት እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

በዚህም አዲስ አበባን ጨምሮ በስምንት ከተሞች የኤሌክትሪክ ፖሎችን የመትከል ሥራዎች ተሠርተዋል። በአሁኑ ጊዜም ከአዲስ አበባ 50 ኪሎ ሜትር ዙሪያ ያሉ ከተሞች የሚያቅፍ የመስመር ዝርጋታ እየተካሄደ እንደሚገኝ አመልክተዋል።

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ በአጠቃላይ ቆጣሪ ገብቶለት የኤሌክትሪክ ኃይል የተጠቃሚ ቁጥር ከአራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን እንደማይበልጥ ታውቋል።

# የወባ ወረርሽኝን ለመከላከል 19 ነጥብ 6 ሚሊዮን አጎበር ተሰራጭቷል

**ማርቆስ በላይ**



አዲስአበባ፡- በተያዘው ዓመት በአገር አቀፍ ደረጃ የወባ ወረርሽኝን ለመከላከል የሚያስችል 19ነጥብ ስድስት ሚሊዮን አጎበር ለተለያዩ ክልሎች መሰራጨቱን የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስትቲዩት የኅብረተሰብ ጤና አደጋ ምላሽ አስተባባሪ አቶ መስፍን ወሰን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተለያዩ ጊዜያት በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚከሰቱ ወረርሽኞች መካከል ወባ አንዱ ነው። በዚህም በተያዘው ዓመት የወባ ወረርሽኝን ለመከላከል የሚያስችል 19 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን አጎበር በተለያዩ ክልሎች ተሰራጭቷል።

እንደ አቶ መስፍን ገለጻ በአገር አቀፍ ደረጃ ከባለፈው ዓመት ከጥር ወር ጀምሮ በተለያዩ ክልሎች የወባ ወረርሽኝ የታማሚዎች ቁጥር ጭማሪ አሳይቷል። ከፍተኛ ጭማሪ ከታየባቸው ክልሎች ውስጥም በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ ክልሎች ላይ በተለይም ከተከሰተው ድርቅ ጋር ተያይዞ ጭማሪ አሳይቷል። በዚህም ተመጣጣኝ ምላሽ በመስጠት ረገድ በትኩረት በመሥራት ላይ ነው።

ከባለፉት አምስት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር ከአፋር እና ሐረሪ ውጪ ባሉት ክልሎች ጭማሪ ማሳየቱን የጠቀሱት አስተባባሪው ወረርሽኙን ለመከላከል የሚያስችሉ የክትትል እና ቁጥጥር ሥራዎች በትኩረት በመሥራት ላይ ነው ብለዋል።

በተለይም በተያዘው ዓመት ለአብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል 19 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን የወባ በሽታን መቆጣጠሪያ አጎበር ስርጭት ተካሂዷል። በዚህም ለኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ እና ሶማሌን ጨምሮ በቂ የሆነ የጸረ ወባ መድኃኒቶችን ለሁሉም ክልሎች መሰራጨቱን ገልጸው፣ ወረርሽኙ ስጋት በሆነባቸው አካባቢዎች በማህበረሰብ ንቅናቄ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በመሥራት ላይ ነው ብለዋል።

በጤና ሚኒስቴር፤ በኅብረተሰብ ጤና ኢንስትቲዩት፣ የክልል ጤና ቢሮዎች እና ባሉት ጤና መዋቅሮች ጋር በመሆን የወባ ታማሚዎችን ማከም፣ ለወረርሽኙ መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉትን የታቆረ ውሃ ማፍሰስ፣ የአጎበር ሥርጭት፣ የቤት ለቤት የመድኃኒት ስርጭት፣ የቅኝት እና የኅብረተሰብ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በመሥራት ላይ መሆኑን ጠቅሰው፣ በአሁኑ ጊዜ የታማሚዎች ቁጥር፣ እንዲሁም የወረርሽኝ መጠን ከፍተኛ ለውጥ በማሳየት ላይ መሆኑን አስረድተዋል።

ወረርሽኙን ለመከላከል የሚያስችል የአጎበር እጥረት አለማጋጠሙን የገለጹት አስተባባሪው በቀጣይ ክልሎች በሚያቀርቡት እና በኅብረተሰቡ ጥያቄ መሠረት ዳሰሳ ተካሂዶ አስፈላጊው የአጎበር ስርጭት የሚከናወን መሆኑን ገልጸዋል።

# በባህርዳር በ743 ሚሊዮን ብር የውሃ ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ ነው

## - በቀጣይ ሁለት ወራት አገልግሎት መስጠት ይጀምራሉ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በባህርዳር ከተማ በ743 ሚሊዮን ብር ወጪ እየተገነቡ ያሉት የውሃ ፕሮጀክቶች በሚቀጥሉት ሁለት ወራት ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምሩ የአማራ ክልል ውሃና ኢነርጂ ቢሮ አስታወቀ።

የአማራ ክልል ውሃና ኢነርጂ ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ወንዳጥር መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የባህርዳር ከተማን የውሃ ችግር ለመቅረፍ በ743 ሚሊዮን ብር እየተገነቡ ያሉት የውሃ ፕሮጀክቶች በመጪው ግንቦት ወር አገልግሎት መስጠት ይጀምራሉ።

በከተማዋ ያለውን የውሃ አቅርቦት እና ፍላጎት ተመጣጣኝ ለማድረግ በጃፓን መንግሥት ድጋፍና በክልሉ ውሃና ኢነርጂ ቢሮ ሁለት የውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ እየተጠናቀቁ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

ኃላፊው እንደገለጹት፤ በጃፓን መንግሥት ትብብር በ650 ሚሊዮን ብር ወጪ በኮኖኬ ተቋራጭነት በአጼ ቴዎድሮስ ክፍለ ከተማ እየተገነባ ያለው የውሃ ፕሮጀክት 98 በመቶ ተጠናቋል። መጋቢት 27 ቀን 2015 ዓ.ም ኮኖኬ ኩባንያ ግንባታውን ላከናወነው የጃፓን ዓለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅት (ጃይካ) ያስረክባል። ጃይካ ፕሮጀክቱን ለቀረጸው አማራ ክልል ውሃና ኢነርጂ ቢሮ ሚያዝያ 1 ቀን 2015 ዓ.ም አስረክቦ የሙከራ ስርጭት የሚጀመር ሲሆን፣ ግንቦት ወር ላይ ሙሉ በሙሉ አገልግሎት መስጠት ይጀምራል።

እንደ አቶ ወንዳጥር ገለጻ፣ በጃይካ ትብብር እየተገነባ ያለው የውሃ ፕሮጀክት ከፍተኛ አቅም ያላቸው ፓምፖች የተገጠሙለት ሲሆን፤ ከዘጠኝ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ንጹህ የመጠጥ ውሃ በማውጣት በ42 ኪሎ ሜትር የቧንቧ መስመር ዝርጋታ ለ147 ሺህ የማህበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

አራት ሚሊዮን እና አንድ ሚሊዮን ሊትር ውሃ የመያዝ አቅም ያላቸው የውሃ ጋኖች ግንባታ ተጠናቋል። እንዲሁም ውሃን ከተለያዩ ጉድጓዶች ተቀብለው ወደ ጋኖቹ የሚልኩ ባለ አንድ ሚሊዮን ሊትር፣ ባለ ሰባት መቶ ሺህ ሊትር እና ባለ ሁለት መቶ ሺህ ሊትር የማቀባበያና የውሃ ማከሚያ ጋኖች ግንባታ እንደተከናወነ ነው ሲሉም ኃላፊው አስረድተዋል።

የውሃ ስርጭትን በትክክል ማቅረብ የሚያስችል እና የውሃ ብክነትን የሚቆጣጠር ቴክኖሎጂዎችም እንደተሠሩለት ጨምረው ገልጸዋል።

ፕሮጀክቱ በሴኮንድ 350 ሊትር ውሃ የማቅረብ አቅም አለው ያሉት አቶ ወንዳጥር፤ የቀጣናውን የውሃ ሽፋን መቶ በመቶ ማሳደግ እንደሚችልም አስታውቀዋል።

ሁለተኛው ፕሮጀክት በአማራ ክልል ውሃና ኢነርጂ ቢሮ በ93 ሚሊዮን ብር ወጪ በአማራ ውሃ ሥራዎች ተቋራጭነት ይባብ አካባቢ ከሚገኘው የጥቁር ውሃ ምንጭ ወደ ከተማው የሚያደርስ የ12 ኪሎ ሜትር የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው የዋና የውሃ መስመሮችን የመቀየር ሥራም ተጠናቋል ብለዋል።

የፕሮጀክቱ ግንባታ 99 በመቶ ተጠናቋል። በመሆኑም የኤሌክትሮ መካኒካል ገጠማው ሲጠናቀቅ ግንቦት ወር ላይ አገልግሎት መስጠት ይጀምራል ብለዋል።

# የብዝሀ ሕይወት ሀብት ከምርምር ባለፈ ለገበያ እንዲውል አልተደረገም

**አስመረት ብስራት**

አዲስ አበባ፡- ብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩትን ጨምሮ አብዛኛዎቹ የምርምር ተቋሞቻችን በዘርፉ ቴክኒካል ምርምሮች ከመሥራት ባለፈ የተሠራው ምርምር ለገበያ እንዲውል ተደርጎ አገር እንድትጠቀምበት ማድረግ እንዳልተቻለ የግብርና ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ ገለጹ።

ሚኒስትሩ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደተናገሩት፣ አገሪቱ ያላትን የብዝሃ ሕይወት ሀብት በበቂ ሁኔታ ባለማስተዋወቋ ሀብቱ የጋን ውስጥ መብራት እንዲሆን አድርጎታል።

ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች እጃችን ላይ ቢኖሩም ሊያመጣው የሚችለው ጥቅም በተገቢው መንገድ ተውዋቆ ኢንዱስትሪዎች ሊወስዱ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ አልተፈጠረም ብለዋል።

አንዳንድ ከብዝሃ ሕይወት ጋር ያሉት ዝርያዎች ውስጥ ኢንዱስትሪ የሚወስዳቸው በጣም መዓዛማ የሆኑ፤ ዘይት የሚወጣቸው ተክሎች መጀመሪያ ላይ አስተዋውቀናቸው ወደ ገበያ የገቡ ናቸው የሚሉት ዶክተር ግርማ፣ ጥረቱ አንድ ምርምር ሠርቶ የሆነ ጆርናል ላይ ከማሳተም የዘለለ ሊሆን ይገባል ይላሉ።

አገር ሸጣ ካልተጠቀመችባቸው ሀብቶች መካከል አንዱ የብዝሃ ሕይወት ሀብት ነው የሚሉት ዶክተር ግርማ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የብዝሀ ሕይወት ዝርያዎች አሉ ቢባልም ዳቦ አለመሆኑን በመረዳት ሀብቱን ለገበያ ማቅረብ ላይ መሥራት ይኖርብናል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የስንዴን ዘር ለዓለም በማስተዋወቅ አስተዋፅዖ ያደረገች አገር ናት ያሉት ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ በሽታን ከሚቋቋሙ የስንዴ ዓይነቶች አንዱ ባለቤት ነች ብለዋል። በዚህም የተነሳ አገሪቱ ከእራሷ የሚተርፍ የስንዴ ምርት ሊኖራት ይገባል ብለዋል።



ዶክተር ግርማ አመንቴ

«ስንዴን ገዝተን መብላት የለብንም፤ ስንዴን እየተረዳን መብላት የለብንም» የሚለው የጠቅላይ ሚኒስትሩ አባባል ትክክል መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ግርማ፣ ይህ በጣም ትክክለኛ ውሳኔ ነው። አቅሙ ስላለን ይህንን ደግፈን ብዙ ቴክኖሎጂ ሰጥተን ከሠራን ውጤታማ እንሆናለን ብለዋል።

አሁን ፖለቲካ የሆነው እኛ በስንዴ ራሳችንን መቻላችን አይደለም፤ ስንዴን ኤክስፖርት እናደርጋለን ስንል የመጣ ጉዳይ ነው ያሉት ዶክተር ግርማ ምክንያቱም ይህች አገር ስንዴ ስትረዳ ስንዴ ስትቀለብ ነው የኖረችው፤ ስለዚህ ይህ ለበርካታ ስንዴን ኢንፖርት አድርገው ለሚጠቀሙ በርካታ የአፍሪካ አገራት ጭምር መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ በመሆኑ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

«ስንዴ ዘንድሮ ከገበያ ወጣ የለም ቢባል እኔን አያስደንቀኝም። ስንዴ ላይ ተአምራዊ ለውጥ አምጥተናል።» የሚሉት ዶክተሩ ከዚህ በኋላ የሚቀረው ሥራ ስንዴ እስኪትረፍርፍ ማምረት መሆኑን አስረድተዋል።

ሌላው ደንን ለኢኮኖሚ አላማ መጠቀም ላይ አገሪቱ ወደኋላ መቅረቷን የጠቆሙት ዶክተር ግርማ ደኖች የካርበን ፑል በመሆናቸው ዓለም ላይ አሁን ካለው የአየር ንብረት ለውጥ አንፃር በዘርፉ ብዙ ሥራ መሥራት ይገባል ብለዋል።

ደን ካርቦንዳይኦክሳይድ ከአየር ይወስድና ኦክስጂን ይለቅልናል። ይህንን ካልኩሌት ማድረግ ይቻላል፤ አንድ ጋርደን ምን ያህል ይመጣል የሚለውን አሳስቦ የሚገኝ ሀብት አለ ብለዋል።

«ይህንን እንደ ፓይለት ፕሮጀክት በባሌ ተራራዎች ላይ ነበር የጀመርነው ኦሮሚያ ውስጥ ባለፈው አመት አርሶ አደሮች ደን በመጠበቃቸው ወደ 300 እና 400 ሚሊዮን ክፍያ ተቀብለዋል። አብዞርቭ ያደረጉት ካርቦን ተለክቶ የዓለም ባንክ 40 ሚሊዮን ዶላር የካርበን ግዢ ከኦሮሚያ ለመፈፀም ቃል ተገብቷል።» ብለዋል።

የተፈጥሮ ደኖች የካርበን ጥቅም አላቸው፤ የኢኮቱሪዝም ጥቅም አላቸው፤ የብዝሀ- ሕይወት ጥቅም አላቸው፤ ሰው ሰራሹ ደን ለኢንዱስትሪ ለወረቀት ለፓልም እና ለብዙ ነገር መጠቀም ይኖርብናል ሲሉም ገልጸዋል። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ደንን በኮሜርሻል ከመጠቀም አንፃር የደን ውጤት አዘጋጅቶ ጥቅም ከማዋል አንጻር አልተሠራም፤ገና ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል ሲሉ አሳስበዋል።

# የድርቅ ስጋት ባለባቸው አካባቢዎች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አካባቢ እንዲኖር ለማድረግ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ኢንቨስትመንት እና ጠንካራ ብዝሃ ሕይወት ያለው ሥነ ምህዳር ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ተሻለ፤ በተደጋጋሚ በድርቅ የሚጠቁ አካባቢዎች ሁሉንም ዓይነት ብዝሃ ሕይወት እንዲኖራቸው ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

አሁን አብዛኛው የተፈጥሮ ሀብት ከደን ወደ ከተማነት፣ ከደን ወደ እርሻነት እና ወደሌሎችም የልማት ሥራዎች እየተቀየረ ነው ያሉት ባለሙያው፤ የብዝሃነት መመናመን ምርታማ አለመሆንን ማስከተሉን እንዲሁም ድርቅን የሚቋቋም አካባቢ እንዳይኖር እና ተደጋጋሚ ድርቅ እንዲኖር ማድረጉን አብራርተዋል።

የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ መጠቀም ተደጋጋሚ ድርቅን ለመከላከል ይረዳል ያሉት ባለሙያው፤ ለረጅም ጊዜ በተፈጥሮ አካባቢ ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ሌላኛው መፍትሄ እንደሆነ ጠቁመዋል።

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የሜትሮሎጂና ሃይድሮሎጂ ረዳት ፕሮፌሰር ቶማስ ቶሮራ በበኩላቸው፤ የደን ጭፍጨፋ፣ የአፈር መሸርሸር እና ልቅ ግጦሽ በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲኖር መንስዔ ሆኗል። የአየር ንብረት ለውጥ ደግሞ የድርቅ ድግግሞሽ እንዲኖር ያደርጋል። ስለዚህ የአየር ንብረት ለውጥ መንስዔን ለመከላከል የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን መሥራት ይፈልጋል ብለዋል።

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ቶማስ ገለፃ፤ በተደጋጋሚ የዝናብ እጥረት በሚከሰትባቸው አካባቢዎች በርካታ ዛፎችን መትከል፣ መስኖ ማስፋፋት፣ ኩሬ እንዲኖር ማድረግ እና የአካባቢውን አየር ንብረትን መቋቋም የሚችሉ ከብቶችን ማዳቀል ችግሩን ለመከላከል ቁልፍ ተግባር ነው ብለዋል።

መንግሥት በአካባቢዎቹ ውሃ የማቆር ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ መሠራት አለበት ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ የዝናብ እጥረት ለርሃብ፣ ለጤና ችግር እና ለበሽታ መስፋፋት ይዳርጋል። ስለዚህ ጉዳዩ እርስ በእርስ በመደጋገፍ መፍትሄ የሚያገኝ በመሆኑ ሁሉም ሰው እንደየአቅሙ የበኩሉን ሚና ሊወጣ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

የድርቅ ስጋት ባለባቸው አካባቢዎች ከፍተኛ ጉዳት ሳይደርስ ፈጣን የመከላከል ተግባር የሚሠራ ቡድን መቋቋም አለበት ያሉት ደግሞ የግብርና እና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሙያ አቶ አዳነ ገዳ ናቸው።

እንደ አቶ አዳነ ገለፃ፤ የዝናብ እጥረት ባጋጠሙባቸው በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች በርካታ ዜጎች ለከፍተኛ ችግር እንደተጋለጡ ይታወቃል። በድርቁ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎችና ከብቶችን ለመታደግ መንግሥት እና ግብረ ሰናይ ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች ያደረጉት ድጋፍ የሚበረታታ እና ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር ነው።

ነገር ግን ሕፃናት፣ እናቶች እንዲሁም ከብቶች ለከፍተኛ ችግርና አደጋ ከመጋለጣቸው በፊት የአደጋውን መጠን መቀነስ ይቻላል። ለዚህም የድርቅ ስጋት ባለባቸው አካባቢዎች ፈጣን የመከላከል እርምጃ ተግባር የሚሠራ ቡድን ማቋቋም ቀዳሚው ተግባር ነው ብለዋል።

እንደ ባለሙያው ገለፃ፤ በተደጋጋሚ ጊዜ የዝናብ እጥረት የሚያጋጥሙባቸው አካባቢዎች ፈጣን የመከላከል ተግባር የሚሠራ ተቋም ከማቋቋም ባለፈ በርካታ ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል። ለምሳሌ በአካባቢው የአየር ለውጥ መንስኤዎችን መቀነስ አስፈላጊ ነው። የዛፎች እና የደን መመንጠር ወይም መቀነስ ለአየር ንብረት ለውጥ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ስለዚህ የአካባቢው ኅብረተሰብ ከእንደዚህ ዓይነት ድርጊቶች ሊታቀብ ይገባል።

# ሰው መሆንን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ብዛት ደክመዋል። ቢንያም ብዙዎች ሊሆኑት ሊያደርጉት የሚመኙትን እርሱ በመኖር አሳይቷል። የመልካምነት ዋሻ የጥሩነት መጠለያ ነው። ጧሪ ለሌላቸው ደጋፊ ለእራሳቸው የደከሙትን ረጂም ጭምር። መፀዳዳት ላልቻሉት ንፅህና መመገብ ለተሳናቸው ምግብ ሰጪ ነው። መንቀሳቀስ አቅቷቸው አልጋ ለተቆራኛቸው አልባሽ አጉራሽ ነው።

የቢንያም ጉዳይ ብዙ የተባለለት፤ ነገር ግን ገና ወደፊትም ብዙ ሊነገርለትና ተሞክሮውም ሊቀመር የሚገባው ትልቅ ዋርካ ነው። ለዛሬ ግን ከዚሁ ጀግና ጎን ተሰልፎ ምርኩዝ ሆኖ የበኩሉን አስተዋፅኦ እያበረከተ ስለሚገኘው ኮሜዲያን እሸቱ መለሰ ልናወጋችሁ ነው።

ኮሜዲያኑ አቅሙን በአምላኩ ትከሻ ላይ ጥሏል። ቀን አዘንብሎበት የሰው ፊት አጥቁሮት ያውቃል። በሰው ፊት መነሳትን የድህነትን ጓዳ ጎድጓዳ አበጥሮ ያውቀዋል። ለእግሩ ጫማ ለዓይኑ ሰው ርቦት ያውቃል።

ኖሮት ያውቃልና ሰው ማጣት ምን ይመስላል ቢባል መልስ አለው። የድህነትን ጎልያድ በመልካምነት ጠጠር መጣል ችሏል። ዛሬ ላይ ፈላጊ ሳይሆን ለሌሎች የሚደርስ ነው። እግዚአብሔር የሚታዘዝ አጥቶ እንጂ ሥራ ለመሥራት ዝግጁ ነው፤ መፍቀድ ብቻ ነው ከእኛ የሚጠበቀው ይላል። በመቄዶንያ ሥራ ፈጣሪ እኔን አከበረኝ እንጂ መቄዶንያማ መጀመሪያም ግዙፍ ተቋም ነው ብሏል። ክብርና ሞገስ በችግርና መከራ መልክ እንጂ በካባ በወርቅ ሀብል መልክ አይመጣም ይላል በተለያየ ጊዜያት ሲናገር።

ኮሜዲያን እሸቱ የዘመኑን መልካም አጋጣሚ ዲጂታሉን ዓለም በመጠቀም ለብዙዎች ደረሰ። ሃይማኖትን ሳይለይ ፆታ ብሔር ሳይገድበው ሊደረስላቸው ለተገባ ሁሉ በቻለው ሁሉ ደረሰ። የቅን አሳቢዎችን ኪስ በመልካምነት እጁ ፈተሸ።

መቄዶንያ በአዲስ አበባ አያት ፀበል መድኃኒዓለም ላይ ከትሟል። በዚሁ ግቢ ውስጥ የሆነ ዘመናዊ ሆስፒታልና ምቹ የአረጋውያን መኖሪያ ሕንፃ እየገነባ ነው። የዚህ ሕንፃ ጉዳይ ነው ኮሜዲያን እሸቱን አገር ጉድ ያሰኘ የመልካምነት ተግባር እንዲከውን ዕድል የሰጠው።

በመቄዶንያ ምክንያት ከ7ሺህ 500 በላይ ነፍሶች ከመኖር ተዋወቁ። እንደ ሰው ተቆጥረው ከጅብ ራትነት ተረፉ። መቄዶንያ ማንኛውም የሕይወት ክፉና ደግ ገጠመኞችን ከአረጋውያኑ ጋር ማሳለፊያ ዕድልን ፈጥሯል። ቤት፣ መኪና፣ የንግድ ተቋም፣ የቤት ዕቃ ማንኛውንም ማውረስ የሚቻልበትን መንገድም ጭምር። በማዕከሉ በመገኘት ተጫጭተው የተጋቡ ወልደው የልጆቻቸውን ልደት ያከበሩ እልፎች ናቸው።

መቄዶንያ አካል ጉዳተኞችና አቅመ ደካሞችን ምቾት ከግምት ያስገባ አዲስ ሕንፃ እገነባለሁ አለ። በዚህም የተረጂዎችን ቁጥር ሃያ ሺህ ለማድረስ ቆርጦ ተነሳ። ሕንፃው የ15 ወለሎች ባለቤት ነው። ለሕክምና ብቻ አንድ ሺህ 200 አልጋዎች አሉት። አዳራሹ አምስት ሺህ ሰው ይይዛል። 120 መኪናዎችን ማቆም ይችላል። ሰውን ከሚፈልገው ስፍራ የሚያደርሱ ሰባት አሳንሰሮች ይኖሩታል። በሦስት ዓመት ከግማሽ ጊዜ ውስጥ ያለእረፍት በመሥራት 70 በመቶ ማጠናቀቅ ቻለ።

የዚህ ሕንፃ መጠናቀቅ ከ7 ሺህ 500 በመነሳት 20 ሺህ ነፍሶች እንዲደረስላቸው መንገድን ይጠርጋል። ለተጀመረው ሕንፃ 888 በሮችን እና 739 መስኮቶችን ለመግጠም ከቅን አሳቢዎች ጋር ተቃጠረ። ይሄኔ ኮሜዲያን እሸቱ ቀበቶውን ታጠቀ። እውቅ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን የሆኑ አርቲስቶችም አጠገብህ ነን አሉ። የቀናት እንቅልፉን ሰውቶ አላማውን አሳካ። በአንድ መድረክ ቆራጥነት መልካም መሆንና ለአላማ መቆም በኮሜዲያኑ ደጅ ደምቀው ተሞሸሩ።

በኢትዮጵያ የእርዳታ ታሪክ ውስጥ ተአምር ተፈጠረ። ያለፈው የካቲት 26 ከቀኑ 9፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ማክሰኞ ሌሊት 7፡30 የቆየ በዶንኪ ቲዩብ (Donkey tube) አማካኝነት በቀጥታ ገቢ ማሰባሰቢያ 200 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ በመሰብሰብ የተሳካ ሥራ ተሠርቷል።

መቄዶንያም እሸቱን የማመስገን ግዴታውን አልረሳም ነበር። በወቅቱ አረጋውያንም ከአፋቸው የምስጋና ዜማ ተደመጠ። እንደ ስምህ እሸት እሸት ብቻ ያብላህ፣ ዘርህ ይብዛ፣ ክፉህ ይራቅ፣ ደግ ይከተልህ፣... ብቻ ብዙ መልካም ቃላት ተሰሙ።

ዶንኪ ቲዩብ (Donkey tube) ኮሜዲያን እሸቱና በስሩ ያሉ ሠራተኞች በመቄዶንያ ምስጋና ተችሯቸዋል። በቀጥታ ስርጭቱ ላይ አዳራቸውን በመሰዋት ያስተባበሩ እውቅ አርቲስቶች እና የሃይማኖት አባቶችም በቢንያም ተመስግነዋል።

ሕንፃው አሁንም አላለቀም። የፊኒሺንግ ሥራው ብቻ 800 ሚሊዮን ብር ይፈልጋል። በሁሉም ክልል 34 ከተሞች ላይ የሚገነቡ መኖሪያዎችም ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ያወጣሉ። መቄዶንያ ዛሬም በአጠቃላይ ሁለት ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ከፍተኛ ወጪ አለበት። ለዚሁ አላማም የቀጥታ ስርጭት የገቢ ማሰባሰቢያ እንዲሁም በቀጣይም ሚሊኒየም አዳራሽ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያሳተፈ ሰፊ የገቢ ማሰባሰቢያ ይዘጋጃል።

ከዚህ ቀደም ድርጅታችን መቄዶንያን በጎበኘበት ወቅት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ እንደተናገሩት፣ መቄዶንያን መደገፍ የነገ ቤትን መሥራት ነው። ይህን ቤት መገንባት ደግሞ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የተሰጠ አደራ ነውና መቄዶንያን ይርዱ ይደግፉ እንላለን።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለግብርና ኢንቨስትመንት ወሳኝ ወቅት!

ኢትዮጵያ የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ለማሳደጉ ስራ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ትገኛለች፡፡ ለዚህም መንግስት ለአፈር ማዳበሪያ እያደረገ ያለውን ድጎማ በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በ2014/15 የምርት ዘመን ሀገሪቱ 15 ቢሊዮን ብር ለአፈር ማዳበሪያ ግዥ ድጎማ አድርጋለች፡፡ በተያዘው 2015/16 የምርት ዘመን ደግሞ ይህ አሀዝ ወደ 21 ቢሊየን ብር ከፍ ብሏል፡፡ ይህም ምርትና ምርታማነቱን ይበልጥ ለማሳደግ እንዲሁም አርሶ አደሩ ከአፈር ማዳበሪያ እየተወደደ መምጣት ጋር ተያይዞ የማዳበሪያ አቅርቦት ችግር እንዳይገጠመው በሚል የተወሰደ ርምጃ ነው፡፡

መንግስት ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት ተከትሎም የግብርናው ምርትና ምርታማነት እየጨመረ መጥቷል፡፡ አንድም ማሳ ጦም እንዳያድር በሚል እየተከናወነ ባለው ተግባር፣ የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት እየተሰፋፋ መምጣት፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቃም መስፋፋትና የመሳሰሉት ለለውጡ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ከዘርፉ ተግዳሮት አንዱ በመሆን የሚታወቀውን የአርሶ አደሮች ማሳ የተበጣጠሰ መሆን ችግርን አርሶ አደሩን በማሳመን ኩታ ገጠም እርሻን በማስፋፋት ግብርናውን ለቴክኖሎጂ አጠቃቀም ምቹ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም በትራክተር መጠቀምን ጨምሮ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ስራ ላይ መዋል እየተቻለ ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባደጉት ሀገሮች እንደሚስተዋለው አንድ አይነት ሰብል የለማባቸው ሰፊፋ የእርሻ ማሳዎችን ማየት የተቻለው አንድም የኩታ ገጠም እርሻ መምጣቱን ተከትሎ ነው፡፡ ሁሉም ጥረቶች የዘርፉን ምርትና ምርታማነት ወደፊት እያራመዱት ይገኛሉ፡፡

በሀገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነው የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ሌላው የዘርፉን ምርትና ምርታማነት በወሳኝ መልኩ ማሳደግ ያስቻለ ተጠቃሽ ተግባር ነው፡፡ በአንዴ ከማምረት ሁለቴና ሶስቴ ማምረት ውስጥ መግባት ብቻውን ትርጉሙ ሰፊ ነው፡፡ ልማቱ ቴክኖሎጂን በሚገባ ለመጠቀም ምቹ ሁኔታ የተፈጠረበት እንደመሆኑም ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በኩል ፋይዳው ከፍተኛ እየሆነ ይገኛል፡፡ በሀገሪቱ ዓመታዊ የግብርና ምርት ላይ እስከ 26 ኩንታል ተጨማሪ ማግኘት የተቻለበት ሁኔታ የተፈጠረበት የምርት ዘመን ለምርትና ምርታማነት እየጨመረ መምጣት ሁነኛ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይህ አሀዝ በዚህ የምርት ዘመን ወደ 52 ሚሊየን ኩንታል እንደሚያድግ ይጠበቃል፡፡

ይህ እድገት እየተመዘገበ ያለው ለምርትና ምርታማነት እድገት ብዙ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ እምቅ አቅሞች ገና ብዙም ባልተነኩበት ሁኔታ ነው፡፡ የግብርና ኢንቨስትመንትን ለእዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሀገሪቱ በግብርና ኢንቨስትመንት በኩል ሊደረስበት የሚፈለገውን ርቀት ተጉዛለች ባይባልም በአንዳንድ ክልሎች በተወሰነ መልኩ እየሄደችበት ትገኛለች፡፡ በዚህ ብቻም የግብርና ኢንቨስትመንትን ፋይዳ መቅመስ ተችሏል ማለት ይቻላል፡፡

ይህን ኢንቨስትመንት አሁን ወደ ማስፋት መግባት ያስፈልጋል፡፡ እየተስፋፋ የመጣው የኩታ ገጠም እርሻ፣ የሜካናይዜሽን ተጠቃሚነትና አገልግሎት ለግብርናው ዘርፍ መቅረብ የጀመረው የፋይናንስ አገልግሎት ሲታሰቡ የግብርና ኢንቨስመንትን ማስፋፋትን ከመቼውም ጊዜ በላይ በዚህ ወቅት ማሰቡ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህ ኢንቨስትመንት ለዚህች ሀገር የግብርና ምርትና ምርታማነት እድገት ወሳኝ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ጥርጥር የለም፤ ያደጉት ሀገሮች ተሞክሮም ይህንኑ ያስገነዝባል፡፡

በቅርቡ «የመሬት አስተዳደርና የአካታችነትና ዘላቂ ልማት ጎዳና» በሚል የተካሄደ መድረክን ዋቢ ያደረገ መረጃ እንዳስገነዘበው፤ የእርሻ ኢንቨስትመንትን በዘመናዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ የግብርና ኢንቨስትመንት ብዙ ችግሮች ያሉበት ቢሆንም፣ ኢኮኖሚውን ሊያሸጋግር ይችላል፡፡ የግብርናው ዘርፍ እንዲዘምንና በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ለማድረግ የግሉ ዘርፍም እንዲሳተፍበት ማድረግ እንደሚገባና ለእዚህም ማበረታቻ እንደሚያስፈልግ በመድረኩ ተጠቁሟል፡፡ የእርሻ መሬትን በዘመናዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ለዘርፉ ምርትና ምርታማነት ዕድገት ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ በሚገባ ለመጠቀም ደግሞ የግብርና ኢንቨስትመንት ያስፈልጋል፡፡ ለግብርና ዘርፍ ምርትና ምርታማነት እድገት የግብርና ኢንቨስትመንት አስፈላጊ ስለመሆኑ የምጣኔ ሀብት እንዲሁም የግብርና ባለሙያዎችም ያስገነዝባሉ፡፡

በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች በግብርና ኢንቨስትመንት ከተሰማሩ ባለሀብቶች መረዳት እንደሚቻለውም ዘርፉ አዋጭ መሆኑን ነው፡፡ ይሁንና ከለውጡ በፊት እንደ ጋምቤላ ባሉ አካባቢዎች ለግብርና ኢንቨስትመንት በሚል የገቡ ባለሀብት ተብዬዎች በፈጠሩት ችግር ሳቢያ ልማቱን ማስቀጠል አልተቻለም፡፡ ሀገርም በእነዚህ ለግብርና ኢንቨስትመንት በሚል ብድር በወሰዱ ባለሀብቶች ለኪሳራ ተዳርጋለች፡፡ ይህ ሁኔታ በግብርና ኢንቨስትመንት ላይ ጥቁር ጠባሳ ጥሎ አልፏል፡፡ ችግሩ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ከመሬት አቅርቦትና አጠቃቀም ጋር በተያያዘም የግሉን ዘርፍ በግብርና ኢንቨስትመንት መሰማራት የሚችልበት ሁኔታ ጠባብ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ በመማር ኢንቨስትመንቱን ማስፋፋት ግን ይገባል፡፡ ባለሀብቱ በዘርፉ ሊሰማራ የሚችልበትን ጠንካራ ስርዓት መዘርጋት ይገባል፡፡

የግብርና ኢንቨስትመንት ሀገሪቱ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እያደረገች ካለችው ጥረት እንዲሁም ዘርፉ ኢኮኖሚውን ለማሻገር ካለው ፋይዳ አኳያ ለግብርና ኢንቨስትመንት ትኩረት የመስጫው ጊዜ አሁን መጀመር ይኖርበታል፡፡ ይህች ሀገር ለግብርና ኢንቨስትመንት ሊውል የሚችል ሰፊ ለም መሬትና ለመስኖ ሊውል የሚችል በቂ የውሃ ሀብት አላት፤ በቂ የሰውም ኃይልም እንዲሁ፡፡ ሀገር ይህን ሁሉ ሀብት ይዛ ስለምግብ ዋስትና ችግር መነጋገሩ ማብቃት ይኖርበታል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው በግብርና ኢንቨስትመንትም ላይ ሲሰራ ጭምር ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ ከመሬት አጠቃቀም ጋር ተያይዞ ያሉ ህጎችን መፈተሽ፤ ኅብረተሰቡን ማስገንዘብ፣ የግብርና ኢንቨስትመንትን ፋይዳ ማስረዳት፣ የግሉ ዘርፍ ከአርሶ አደሮች ጋር በጥምረት ሊሰራ የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ላይ በትኩረት መስራት ያስፈልጋል፡፡ የግብርና ኢንቨስትመንት በሌሎች ሀገሮች እያስገኘ ያለውን ጥቅም፣ በምን አይነት መልኩ እየተፈጸመ ስለመሆኑ ተሞክሮዎችን መቀመርና በሥራ ላይ ማዋልም ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዓባይ ለኢትዮጵያ ወንዝ ወይስ ሕይወት?

ሚሊዮን ሺበሺ

‹‹ዓባይ ለግብጽ ሕይወት ነው›› የሚለው የግብጾች ተደጋጋሚ ትረካ መፈክሩን ዓለም አቀፍ አድርጎታል። ለአንዳንዶች ዓባይ የምርምር የግብጽ ሕይወት ሲመስላቸው አንዳንዶች ደግሞ እውነታውን ውስጣቸው ቢያውቅም ለኢትዮጵያ ባላቸው አሉታዊ አመለካከት ብቻ እውነት አስመስለው ይተርኩላቸዋል። እዚህ ላይ ትልቁ ችግር ዓባይ ለግብጽ ሕይወት ነው መባሉ ብቻ ሳይሆን ፤ ችግሩ ለኢትዮጵያም ከግብጽ በላይ ሕይወት መሆኑን መረዳት አለመፈለጋቸው፤ የዓባይ ባለቤት ግብጽ እስከምትመስል ድረስ የትርክት መዛባት መፍጠራቸው ነው።

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ከስድስት ይሁን አምስት ዓመታት በፊት በዓባይ ጉዳይ ላይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁራንን ያወያየበት አንድ መድረክ ላይ ታድሜ ነበር። በወቅቱም ምሁራኑ የዓባይን ጉዳይ ከዓለም አቀፍ ሕግ አንፃር፣ ከስምጥ ሸለቆ ካለው ርቀት አንፃር፣ ከታሪካዊ ውዝግቦች አንፃር... አንስተው ትንታኔ ሰጥተውበታል።

ከተሰጡት ትንታኔዎች አንድ ቀልቤን የገዛውና ከዚያ በፊት ሰምቼው የማላውቀው ፤ ግብጽ ሁል ጊዜም ከዓባይ ውጭ ምንም የውሃ አማራጭ የሌላትና ህልውናዋ በዓባይ ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆኑን ስትገልጽ ብትኖርም ፤ ከየትኛውም አገር በላይ የከርሰ ምድር ውስጥ ውሃ ያላት አገር መሆኗን ነው።

በእርግጥ እጅጋየሁ ሽባባው(ጂጂ) እንዳለችው ግብጾች የሚበሉትም የሚጠጡትም ውሃ ነው። ዓባይን በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎቻቸው ውስጥ ሁሉ አስገብተው ሕይወት አድርገውታል። የትምህርት ሥርዓታቸው ሁሉ በዓባይ የታቃኘ መሆኑን ባለሙያዎች ይናገራሉ። ከመዋዕለ ሕጻናት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ድረስ ዓባይ የአፍ መፍቻቸው እና የጥናትና ምርምር ምንጫቸው ነው።

የዓባይ ባለቤት ወደሆነችው ኢትዮጵያ ስንመጣ ግን የትርክት የበላይነት ተወስዶባታል። ግብጾች ዋሽተው ዓለምን ለማሳመን ሲሞክሩ ኢትዮጵያውያን ግን ተፈጥሯዊና ነባራዊ ሀቁን እንኳን ለመናገር ስንሸኮረመም ረጅም ዘመናት አስቆጥረናል። በወንዙ ውሃ ላይ ትንሽ መነቃቃት የፈጠርነው ከታላቁ ህዳሴ ግድብ የመሰረት ድንጋይ መጣል ወዲህ ነው።

እሱም ቢሆን በቂ አይደለም። በቂ ባለመሆኑም ግብጽ ወቅት እየጠበቀች የዓለምን ቀልብ ይገዛልኛል የምትለውን ሁሉ ይዛ ብቅ የምትለው። የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተገቢውን ምላሽ የሰጠባት የሰሞኑ ንግግሯም የዚሁ አካል ነው።

ዓባይ ለኢትዮጵያ ወንዝ ብቻ ሳይሆን ሕይወት ነው። ሕይወት ነው ስንል ከመሬት ተነስተን አይደለም። ይህን ሀቅ ለማወቅ ዓለም አቀፍ ‹‹ጆርናል›› ማገላበጥ ወይም የብራና ታሪኮችን ማፈላለግ አይጠበቅብንም። የኢትዮጵያን ሕዝብ ማህበራዊ ስሪት ማየት በቂ ማስረጃ ነው። በመኖር የምናውቀው ታሪክ ነው። ዛሬም እየተኖረ ያለ ማህበራዊ መስተጋብር ነው።

በገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍል ያለውን ማህበረሰብ የሕይወት መስተጋብር ካየን ከዓባይ ጋር የተቆራኘ ነው። በየመድረኩ ሲነገር የምንሰማው አንድ ነገር አለ። ‹‹ዓባይ ለዘመናት ለፉከራ እና ለሽለላ ብቻ ስንጠቀመው ኖረናል›› የሚል። ይህ ፉከራና ሽለላ ዝም ብሎ አልመጣም፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ቁርኝት ስላለው ነው። እንዲያውም በምሁራን ከተሰሩ ጥናቶች በላይ ይህ የሽለላና ፉከራ ትውፊት የኢትዮጵያን ሕዝብና የዓባይን ግንኙነት ያሳያል።

ተረቶች፣ ሐተታ ተፈጥሮዎች፣ አፈ ታሪኮች፣ የሕዝብ ስነ ቃሎች... ከዓባይ ጋር የተያያዙ ናቸው። ዓባይ በዘመናዊው ሥርዓተ ትምህርታችን ውስጥ በቂ ቦታ ባይሰጠውም በልማዳዊ ትምህርቶች ውስጥ ግን ሰፊ ቦታ አለው። በገበሬው ሕይወት ውስጥ ሰፊ ቦታ አለው። ገበሬው መከፋቱን፣ መደሰቱን፣ ማፍቀሩን፣ መጥላቱን... ሁሉ የሚገልጸው በዓባይ አስመስሎ ነው። የስነ ቃሎችን ይዘት በዓይነት በዓይነት ሌላ ጊዜ በሌላ ጽሑፍ የምንመጣባቸው ይሆናል።

እነዚህ ነገሮች ለምን ሆኑ ከተባለ ዓባይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወት ስለሆነ ነው። ምሳሌያዊ ንግግሮች ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርዱ ሲወራረዱ የመጡ ናቸው። ዓባይ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የነበረውን ቦታ ያሳያል። በዓባይ ተምሳሌትነት ግዝፈትን፣ ኃይለኝነትን፣ አይደፈሬነትን፣ አንዳንዴም ቻይና ታጋሽነትን ሲገልጹበት ኖረዋል።

ስንፍናችን የት ጋ ነው ከተባለ ፕሮጀክቱን ቀድመን አለመጀመራችንና ከተጀመረ በኋላም አለማፋጠናችን ብቻ አይደለም። ስንፍናችን ዓባይ በዚህ ልክ ለኢትዮጵያ ሕይወት መሆኑን አለማሳየታችን ነው። ግብጾች በሰው ሰራሽ መንገድ የፈጠሩትን ትርክት እኛ በተፈጥሮ በተሰጠን ፍጥረታዊ እውነታ ገዝፈን መሸፈን አለመቻላችን ነው።

እንዲያውም ከጥቂት ጊዜያት ወዲህ እንቅስቃሴዎች ባይጀመሩ ኖሮ በአሁኑ ትውልድ የመታወቅ ዕድሉ ጠባብ ነበር። ምክንያቱም ዓባይ በብዛት ስሙ የሚነሳው በገጠሩ ክፍል ነው፤ ከተሜነት እየተስፋፋ ሲሄድ ከዓባይ ጋር የሚኖረው ቁርኝት እየራቀ ይሄዳል። ስለዚህ የተማረው ክፍል በመገናኛ ብዙኃንና በየመድረኮች ማሳወቅ አለበት። የከተሜው ማህበረሰብ ዓባይን በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴው ውስጥ የሚያስታውስባቸው ነገሮች መኖር አለባቸው።

ዓባይን ከሚያስተዋውቁ ነገሮች አንዱ ደግሞ ስያሜዎች ናቸው። የፋይናንስ ተቋማት፣ የተለያዩ ፋብሪካዎች፣ የመገልገያ ንግድ ቤቶች፣ ተሽከርካሪዎች... የመሳሰሉት በየቦታው የመታየት ዕድል ስላላቸው ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው።

ዓባይ እንደ ስሙ ሰፊ ነው የሚባለው ለዚህ ነው። የምንጠቀምበት አጋጣሚ ከውሃ ጋር ብቻ የተያያዘ አይደለም። ዓባይ የሚለው ቃል ከወንዝነት ያለፈ ነው። ትልቅነትን፣ ዘላቂነትን፣ አያልቄነትን... ለመግለጽ የምንጠቀመው ነው። ‹‹ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል›› የሚባለው አባባልም ትልቅነትንና አያልቄነትን ለመግለጽ ነው።

ወዲህ ደግሞ ወደ ታላቁ የህዳሴ ግድብ እንምጣ። በየዘመኑ ያለ ትውልድ የሚወደስበት ታሪክ አለው። ለምሳሌ የዓድዋ ትውልድ እነሆ ከመቶ ምናምን ዓመታት በላይ እየተወደሰ ነው፤ በስማቸው እየፎከርን ነው። ይህ የህዳሴ ግድብ ደግሞ የዚህ ትውልድ ሕይወት አካል ነው። ለሺህ ዘመናት ሳይደፈር የኖረውን ዓባይ የደፈረ እና ግድብ የሰራ ነው። ስለዚህ በአባቶቻችን ታሪክ እንደምንኮራው ሁሉ የእኛም የሕይወት ታሪክ ትልቁ ትርክት ነው።

ለጊዜው በፕሮጀክት ስም ይጠራ እንጂ ፤ በዘመናት ውስጥ ከታሪክም በላይ ሕይወት ነው። ሕይወት ነው ሲባል በዚህ ፕሮጀክት የሚድኑ ነፍሶች ይኖራሉ ማለት ነው። እነዚያ በጭስ ዓይናቸው የሚሟሟ እናቶች ሕይወት ይቀየራል ማለት ነው። የሚደርስባቸው የጤና ችግር ይቀረፋል ማለት ነው። አሁን ዘመኑ የኤሌክትሪክ ነው። ቤት ውስጥ መብራት ሲጠፋብን ጾማችንን ልናድር እንችላለን። ስለዚህ ሕይወት ሆኗል ማለት ነው።

ግብጾች ዓባይን ‹‹ሕይወታችን ነው ›› ያሉት ከዓባይ ወንዝ ላይ በብርጭቆ እየጨለፉ የሚጠጡት ሆኖ አይደለም። በዘመናዊ መንገድ የሚበላም የሚጠጣም ስላደረጉት ነው። ለኢትዮጵያ ደግሞ ከዚህም በላይ ነው፤ ምክንያቱም ከታሪካችንና ከማህበራዊ ስሪታችን ጋር የተቆራኘ ስለሆነ!።

በዚህና ከዚህም በላይ በሆኑ ዛሬ ላይ ባልዘረዘርኳቸው ምክንያቶች ዓባይ ለኢትዮጵያ ወንዝ ብቻ ሳይሆን ሕይወት ነው!

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

# የፋሽን ዳራዎች በስነ-ውበት ሲቃኙ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**



ፋሽን እንደግል ምርጫ እንደመሆኑ ውበትና አንድናቆትም እንደየሰው እይታ ነው። በመሆኑም ፋሽን ወጥ የሆነና ይሄ ነው የሚባል ስምምነትም ሆነ ቅርጽ የለውም የሚለው ሃሳብ ብዙዎችን ያስማማል። አንድ ነገር ግን ሁሉንም ሊያስማማ ይችላል። ማንም ሰው ቢሆን የትኛውንም ፋሽን ሲከተል ዋነኛ አላማው በሰዎች ዘንድ ቆንጆ ሆኖ መታየት ነው። ታዲያ እዚህ ጋር አንድ ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። ሁሉም ፋሽኖች በእያንዳንዱ ሰው ዘንድ እኩል ውበትን ማላበስ ይችላሉ? ብዙዎችን የሚያስማማው መልስ አይሰጡም ይሆናል። ምክንያቱ ደግሞ የምንከተለው እያንዳንዱ የፋሽን አይነት ውብ ሆኖ አምሮብሃል፣ አምሮብሻል የሚያስብለው የፋሽኑ የጥራት ደረጃ፣ የወጣበት የገንዘብ መጠን ወይንም ሌላ አይደለም። ጉዳዩ የተፈጥሮና የስነ-ውበት ነው። ፋሽን የግዴታ የሚያስብል ህግ ባይኖረውም የስነ-ውበት ህግ አለው። አብዛኛውን ጊዜ በፋሽንና ሞዴሊንግ ውድድሮች ላይ እነዚህ ህጎች እንደ መስፈርት ይታያሉ። እነዚህን ህጎች የተሻለ በጠበቅን ቁጥር የተሻለ ቆንጆ ሆነን እንታያለን። በፋሽናዊ እይታ ውስጥ የሚያምር ፊት ስላለን ብቻ ቆንጆ አያስብለንም። የማያምር ፊት ስላለንም አስቀያሚ አይደለንም። ሁሉም ነገሮች የሚወሰኑት ያለንን ነገር በምንጠቀምበት መንገድ ነው።

ተፈጥሮ የሰጠችንን ጥሩም ይሁን መጥፎ የውበት ገጽታ በሚመጥን የፋሽን አይነት ጠብቆ ማቆየትም ሆነ ማከም እንችላለን። የስነ-ውበት ህጎቹ ባለን የሰውነት ቅርጽ፣ ቁመት፣ የቆዳ ቀለም፣ አቋም እንዲሁም ባለን የሰውነት ክብደት ላይ የተመሰረቱ ናቸው። እነዚህ ነጥቦች በእያንዳንዱ የፋሽን ስርዓት ውስጥ ትልቅ ሚና አላቸው። አንዳንድ ጊዜ ወደ ቡቲኮች ጎራ ብለን የሚያምር ልብስ ገዝተን እንመጣና ስንለብሰው ግን በእኛ ላይ የማያምር አይነት ሆኖ ልናገኘው እንችላለን። አንዳንዴ ደግሞ እኛ አስጠልቶን የጣልነውን ለሌላ ሰው ሰጥተነው አሊያም ድንገት ካስቀመጥንበት አንስቶ ለብሶት ስናየው እስከዛሬ ያልታየን የልብሱ ውበት ይገለጥልና አዲስ ይሆንብናል። ስለዚህ በአንዱ እያማረ በሌላው ደግሞ ውበቱ የሚደበቅበት ምክንያት የህጎቹ የስነ-ውበት ሚስጥር ነው። ታዲያ እነዚህን ህጎች በመከተል የእኔን የውበት ቁልፍ እንዴት ነው ላገኘው የምችለው አሊያም የማውቀው ብለን ልንጠይቅ እንችላለን። ነገር ግን ምላሹ ቀመር አሊያም ስሌት አይደለም። ይህን ለማግኘት ስለ ተፈጥሯዊ የቀለማት ውህደት በጥቂቱም ቢሆን ማወቅን ይጠይቃል። ለምሳሌ ያህል በእነዚህ ህጎች ውስጥ የቀለማት ህግጋቶች ይገኙበታል። ቀይ ሰው ከወገብ በላይ ቀይ ቀለም ያላቸውን አልባሳት ባይለብስ ይመከራል። የፊቱና የልብሱ ቀለም በሚመሳሰልበት ወቅት የሰውየው መልክ ይደበቃል አሊያም የልብሱ ውበት ይደበዝዛል።

ይሄ ደግሞ ለእይታ የማይማርክ ገጽታን ያጎናጽፋል። እግረ ቀጭን የሆኑ ሰዎች ከቁምጣና በጣም ጠባብ ከሆኑ አልባሳት ይልቅ ሰፋ ያሉ ሱሪዎችን ቢያዘወትሩ የተሻለ የውበት ገጽታ ይኖራቸዋል። ሌላው ደግሞ ሱሪ፣ ጫማ፣ ሸሚዝ፣ ኮት ወዘተ..የምንጠቀምበት መንገድ በራሳቸው እይታዊ ውበትን መፍጠር ይችላሉ። ምን አይነት ሱሪ ከምን አይነት ጫማ ጋር ብንለብሰው የተሻለ ውበት ይኖረዋል...ለመረጥነው ሱሪ አሊያም ሹራብ ከቀለማትም ሆነ ከሌሎች ነገሮች አንጻር የተሻለና አብሮ ሊሄድ የሚችል ነገር መምረጥ ከቻልን አለባበሳችንም ጥሩና ያማረ መሆን ይችላል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለማት በአንድ ላይ መሰባጠራቸውና ከላይ እስከታች የተሰባጠሩበት መንገድ ለእይታ የተለየ ውበትን ይፈጥራሉ። ነገር ግን ቀለማቱ ለየብቻ ቢሆኑ አሊያም ቅደም ተከተላቸው በእንዲህ አይነት መልኩ ባይሆን ኖሮ ያንን ውበት ላናየው እንችላለን።

የምንከተላቸው ፋሽኖች ስኬታማና ሁሌም ተመራጭ ለመሆን ምንጊዜም የራሳችንን ትክክለኛ ምርጫ ማድረግ ይኖርብናል። ስታይሎቻችን የተፈጥሮ ውበታችንን አጉልተው የማውጣትም ሆነ የመደበቅም ኃይል አላቸው። አንዲት ጸጉሯ ከፊት ገባ ያለ ቆንጆ ሴት፣ ጸጉሯን ሹርባ ብትሰራው የውበት ገጽታዋን ሊያበላሽና ቁንጅናዋን ሊሰውረው ይችላል። ነገር ግን ከዚህ ይልቅ የጸጉሯ ስታይል ፓንክ ቢሆን የተሻለ ይሆናል። ጸጉሯን ወደፊት በመድፋት ገባ ያለውን ክፍል የሚሸፍንላትን ስታይል በመጠቀም ክፍተቱን ልትሞላው ትችላለች። አብዛኛውን ጊዜ ወንዶች ጸጉራቸው መመለጥ ሲጀምር ኮፊያ ያዘወትራሉ። ራሰ በራነት በተፈጥሮ የሚፈጠር ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ይህ ተፈጥሮ ለአንዳንዶቹ ውበትና የሚያምር ገጽታን አላብሷቸው እንመለከታለን። እዚህ ጋር ከላይ ያነሳነውን የሰውነት ቅርጽ የምትለዋን የስነ-ውበት ህግ እናነሳታለን። መመለጥ የሚያምርባቸውና የማያምርባቸው እነማን ናቸው ካላችሁ፤ ምላሹ የሚገኘው ሰዎቹ ባላቸው የራስ ቅልና የፊት ቅርጽ የሚወሰን ይሆናል። ሁልጊዜ ባይሆንም፣ አብዛኛውን ጊዜ ትልቅ የራስ ቅል ያላቸው ሰዎች እምብዛም ጸጉር ላያምርባቸው ይችላል። በሴቶቹ ዘንድም ከጸጉር ይልቅ የጸጉር ቁርጥ የሚያምርባቸው እንዳሉ አስተውለን ሊሆን ይችላል። በዚያው ልክ ደግሞ ጸጉራቸውን ከመቆረጥ ይልቅ ሲያሳድጉ፣ ሹሩባና የመሳሰሉትን የጸጉር አሰራሮች ሲከተሉ የሚያምርባቸውም እንዲሁ ሞልተዋል። እነዚህ ምሳሌዎች ተፈጥሮ ምን አይነት የፋሽን ሳይንስን መከተል አለብን የሚለውን ሀሳብ ያጠናክራሉ። ስለዚህ በፋሽኖቻችን ውስጥ ውበትን ለመፍጠር በምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሁልጊዜም ተፈጥሯችንን ያማከሉ መሆን አለባቸው።

ፋሽን ጥበባዊ ሳይንስ እንደመሆኑ የፋሽን ተከታዮች ስንሆን ደግሞ አስቀድመን ሳይንሱን ልናውቅ ይገባል። በሳይንሱ ውስጥ ያሉት እነዚህ ህጎችም ከሰው ሰው እንደሁኔታው የሚለያዩ ናቸው። እነዚህን ነገሮች ለማወቅ ማስተዋልን እንጂ ብዙ ማሰብም ሆነ መጨነቅና መጠበብ የሚጠይቁ አይደሉም። ምናልባትም አብዛኛዎቹ የምናውቃቸው ነገር ግን የማናስተውላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ሁሉም ሰው ቆንጆና ውብ ሆኖ መታየት ይችላል። ሁሉም ሰው ደግሞ የራሱ የሆኑ የውበት ምንጭና ሊከተላቸው የሚገባው የራሱ የሆኑ ስርዓቶች አሉት። ትልቁ ነገር ካለን ነገር በመነሳት ለእኛ የሚመጥነውን መፈለግ ነው።

# ትዝብት/ ማረፊያ

# ስድብ ያስመሰልጠን ምልክት ነው

**ስምስም መንግሥቱ**

በዚህ ዘመን ከሥራም ሆነ ከተለያየ ጉዳይ ፋታ ሲገኝ ምን ተባለ? ለማለት ብዙዎች ከሰው ምላሽ አይጠብቁም። የእጅ ስልክ አንስቶ ማህበራዊ ድረ ገጾችን(ሶሻል ሚዲያ) ፈተሽ ፈተሽ ማድረግ በቂ ነው። ማህበራዊ የትስስር ገፆች ከእውነቱ ውሸቱ የበዛባቸው ነው ቢባል እንኳን ሳይፈልጉም ቢሆን መጎብኘት የተለመደ ነው። እርግጥ ነው ሰልችቷቸው እራሳቸውን ለመገደብ የሞከሩም አይጠፉም። ማን ምን አለ ብለው ለመታዘብ ብቻ ጎራ የሚሉም አሉ።

የዛሬው ትዝብቴ ግን ከነዚህም የተለየ ነው። ለመሳደብ ወደ ማህበራዊ ሚዲያው ስራዬ ብለው ጎራ የሚሉ ሰዎችን ይመለከታል። ስራዬ ብለው ለመሰዳደብና ለመበሻሸቅ ወደ ማህበራዊ ሚዲያው ብቅ የሚሉ ግለሰቦች እዚሁ አገር ውስጥ ቢኖሩም በርካቶቹ በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን ናቸው። እርግጥ ነው ማህበራዊ ሚዲያዎችና ተከታዮቻቸውን ተጠቅመው አገርና ወገንን የሚጠቅም ለስጋም ለነብስም እረፍት የሚሰጥ አስደማሚ የረድኤት ተግባራትን የሚሰሩ ብዙዎች አሉ። ከእነሱ በተቃራኒ ስራዬ ብለው ለስድብ የተሰማሩ ግለሰቦች ቁጥር ግን ቀላል አይደለም።

በነዚህ ግለሰቦች ዘንድ የፖለቲካ፣ ብሔር ምናምን ጉዳዮች የመሰዳደቢያ አጀንዳዎች መሆናቸው የተለመደ ነው። አስገራሚው ነገር ከዚህ በተለየ ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ አሳድጋና አስተምራ አሁን ለሚገኙበት ደረጃ ያበቃች አገር ጭምር የመሰዳደቢያና መበሻሸቂያ አጀንዳ መሆኗ ነው። ይህ ደግሞ እኛ ጋር እንጂ በሌላው ዓለም ስለመኖሩ እንጃ።




እውነት ለመናገር እንደዚህ አይነት ግለሰቦች በስደት አገር ጥለው፣ ባህር ተሻግረው በባዕድ አገር የሚኖሩበትን ምክንያት ስተዋል። በርካታ ኢትዮጵያውያን በፖለቲካ ምክንያት መሰደዳቸው ባይካድም እጅግ ብዙ የሆኑት በኢኮኖሚ ችግር ሌት ተቀን ለፍተው የራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ሕይወት ለመለወጥ ነው። በማህበራዊ ሚዲያው ለስድብ የሚቀድሙትም እኚሁ መሆናቸው ነው አስገራሚው።

ከተማ መኖርና የከተማ ሰው መሆን ይለያያል። የሰለጠነ ዓለም መኖርና ስልጡን መሆንም እንደዛው። በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የማህበራዊ ሚዲያ ብሽሽቅ የምንታዘበው ነገር ግራ ያጋባል። በየትኛውም ጉዳይ ላይ መሰዳደብ ሃሳብን በነፃነት መግለፅ ተደርጎ እስከመቆጠር፣ እርስበርስ ከፍ ዝቅ ተደራርጎ መዘላለፍ እስከ ድብድብ እስካልደረሰ ሙብትና የስልጣኔ መገለጫ እየተደረገ ተለምዷል። ከአገር ርቄያለሁ ብሎ እትብቱ የተቀበረበትን አገርም ይሁን ግለሰብ ከጥላቻም የዘለለ የፈለጉትን መናገር ነፃነትን እንደማጣጣም ተደርጓል።

ነፃ ንግግር ማለት የጥላቻ ንግግር ማለት እንዳልሆነ በሰለጠነ ዓለም እየኖሩ መዘንጋቱ ይበልጥ አስገራሚ ነው። ነፃነት ሌሎችን መስደቢያ ወይም ማሸማቀቂያ ፍቃድ አይደለም። ነፃነት ከባድ ኃላፊነት ነው። ነፃነት ስድነት አይደለም። ነፃነት ገደብ የሌለው እንዝላልነትም አይደለም። ነፃነት ገደቡም ሆነ ኃላፊነቱ ሕሊናዊ ነው። ነፃነትን በአግባቡ ለመጠቀም እውቀት ይፈልጋል፤ ስነምግባር ግድ ይላል።

በነፃነት ስም ሌሎችን የሚያጥላላና ማንነታቸው ላይ የስድብ ናዳ ማውረድ የነፃነትን እውነተኛ ትርጉም መሳት ነው። ዘመኑ የዕውቀት ነውና የሃሳብ ልዩነትን በሃሳብ ፍልሚያ ብቻ መታገል የስልጣኔ ምልክት ነው። እኔ ብቻ ነኝ ልክ፣ እኔ ብቻ አንደኛ፣ እኔ ብቻ ልጠቀም፣ ሌላው የራሱ ጉዳይ የሚል ራስወዳድ አስተሳሰብ ያልበሰለ ሃሳብ ነው። ብዝሀ ሃሳብን ማክበርና የሌሎችን ማንነት መቀበል የዘመናዊነት ምልክት ነው። አውሮፓውያን ከጨለማው ዘመን ወደ ሕዳሴው ዘመን የተሸጋገሩት ለብዝሀ ሃሳብ እውቅና በመስጠት ነው። ከጥላቻ ምንም እንደማይገኝ በመረዳታቸው ነው አሁን ለደረሱበት ሥልጣኔ ብዝሀ ሃሳብን በነፃነት የሚያንሸራሽሩት። በሃሳብ ተከራክረው፣ ተጨቃጭቀውና ተፋልመው ተቃቅፈውና ተጨባብጠው የሚለያዩት ሰውየው ላይ ሳይሆን ሃሳቡ ላይ በማተኮራቸው ነው።

ፍቅር የጥላቻ መድኃኒት ነች። ሌላውን የሚጠላ ራሱን አይወድም። ራሱን የሚጠላ እንዴት ሌላውን ሊወድ ይችላል? ፍቅር በማድረጉ፣ ለሌሎች ቅን በማሰቡ፣ ደግ ሥራ በመስራቱ የሚደሰት እንጂ የሚፀፀት ማንም የለም። ሌሎችን እንደራስ ማየት የሚያረካ እንጂ አያስቆጭም። ሰው ጥሪው ለፍቅር እንጂ ለጥላቻ አይደለም። የጥላቻ ንግግር ጠላትን ያበዛል፣ ሰላምን ይነሳል እንጂ ወዳጅን አያተርፍም፤ ፍቅርንም አያመጣም።

ሌሊሳ ግርማ መጋቢት 2011 ዓ.ም. በታተመው በፍትህ ቁ.21 መፅሔት ላይ ስለነፃነት ሲናገር እንዲህ ይለናል፡-

‹‹ነፃነት ነፃ አይደለም። የዕውቀትን ዋጋ ያስከፍላል። ዕውቀት መዳረሻ አይደለም። ዕድሜ ልክ የሚደረግ ጉዞ ነው። ሰው የመሆን ጉዞ!››

አዎ! ነፃነት እውቀት ይፈልጋል። አለበለዚያ ነፃነት ራሱ ነፃ አይሆንም። ነፃነት መዳረሻው ሰው መሆን ነው። ሰው መሆን ደግሞ ከዘረኝነት፣ ከጥላቻ ንግግር አስወጥቶ ከሰብዓዊነት የሚያገናኝ መሠረት ነው። ሰው ‹‹እውነተኛ ሰው›› ከሆነ ሌላውን እንደራሱ ያያል እንጂ በጥላቻ ንግግር ሰውነቱን አያበላሽም። ሰው ክቡር ሆኖ ሳለ እንስሶችን መምሰል የለበትም።

ወዳጆች ሃሳብ ላይ እንጂ ማንነት ላይ አናተኩር! ነፃነትን ለበጎ ነገር እናውለው። የጥላቻ ንግግር ለሰዳቢውም ለተሰዳቢውም አይጠቅምም። ቴክኖሎጂውን ለበጎ ነገር ከተጠቀምንበት ሃሳብን የሚያሳድግ፣ ሕሊናን የሚያበስል፣ ወደፊት የሚያራምድ መልካም ትምህርት ልናገኝበት እንችላለንና።

# ግብር መክፈል ለሀገር መታመን ነው

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

በመዲናችን አዲስ አበባ ሰሞኑን "ግብር ለሀገር ክብር" በሚል መሪ ሀሳብ የገቢ ንቅናቄ ማስጀመሪያና ለግብር ከፋዮች እውቅና አሰጣጥ ፕሮግራም ተካሂዷል፡፡ በዚህ ዝግጅት ላይ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ደመቀ መኮንን፣ የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እና ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ተጋባዥ እንግዶች የፕሮግራሙ ታዳሚ ሆነዋል፡፡

በዝግጅቱ ላይ አቶ ደመቀ መኮንን ንግግር ያደረጉ ሲሆን፤ በንግግራቸውም "የተጀመረውን የሀገር እድገት ለማስቀጠል አሰራርን በማበልጸግ በግልጸኝነት የተሞላ የግብር አሰባሰብ ስርዓት ያስፈልጋል" ብለዋል፡፡ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፤ ግብርን በወቅቱ እና በኃላፊነት መክፈል የከተማችንን ብሎም የሀገርን ገቢ የማመንጨት አቅም እንደሚያሳድግ አመልክተዋል፤ ግብርን በታማኝነት መክፈል የስልጡንነት እና የታማኝነት ምልክት መሆኑንም በወቅቱ ባስተላለፉት መልእክታቸው አስታውቀዋል፡፡

በዝግጅቱ ላይ ይሄን መሰል መልዕክቶች ከማስተላለፍ ባለፈ፤ በ2014 በጀት አመት ሞዴል ግብር ከፋይ ለሆኑም 300 ለሚጠጉ ታማኝ ግብር ከፋዮች እውቅና ተሰጥቷል፡፡ ይሄ ደግሞ የግብር ሥርዓት ተገዢነትን ከማጎልበት በተጓዳኝ፤ ሌሎች ወደ ስርዓቱ እንዲገቡ የሚያነሳሳ መልካም ተግባር ነው፡፡ ይሁን እንጂ በእለቱ እውቅና የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች ቁጥር ሲታይ አዲስ አበባ ውስጥ ካለው የሕዝብ ቁጥርና የግብር ከፋይ መጠን ጋር ሲነጻጸር በቂ አይደለም፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ የገቢዎች ቢሮም በቀጣይ ከዚህ ቁጥር የሚልቁ ታማኝ ግብር ከፋዮችን ለማፍራት እንደሚተጋ ነው በዚሁ መድረክ ላይ ቃሉን የሰጠው፡፡

ቢሮው እንዳስታወቀው፤ በበጀት አመቱም 100 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ እየሰራ ነው፡፡ ይሄን ከማሳካት አኳያም ባለፉት ሰባት ወራት ለመሰብሰብ ከአቀደው 59ነጥብ11 ቢሊዮን ብር ውስጥ 58ነጥብ43 ቢሊዮን ብር ሰብስቧል፡፡ ይህም ከእቅዱን 98ነጥብ8 በመቶ ነው፡፡

በንቅናቄ መድረኩ ላይ እንደተገለጸው፤ በአዲስ አበባ ብቻ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ግብር ከፋዮች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 300 ያህሉ ብቻ ተገቢውን መረጃ በማሟላት ግብራቸውን በወቅቱ እየከፈሉ ይገኛሉ። ይህ የሚያሳየው እንደ ሀገር ያለን የግብር አሰባሰብ ስርዓታችን ደካማ መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም ለአንድ ሀገር ዜጎች ግብርን በወቅቱና በታማኝነት መክፈል ግዴታ ነው። ከዚህም ባለፈ ዜጎች ለሀገር የሚታመኑበት ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር የሚገልጹበት ነው።

አሁን ባለው ሀገራዊ እውነታ አብዛኞቹ ግብር ከፋይ ዜጎቻችን ህግና ስርዓትን ጠብቀው የሚጠበቅባቸውን ግብር በወቅቱና በታማኝነት የሚከፍሉ አይደሉም። ከዚህ ይልቅ ስለልማት ስራዎች መጓደልና ስለድህነት አብዝተው የሚያወሩና በዚህም መንግስትን ተጠያቂ ለማድረግ የሚሞክሩ ናቸው።

ይሁን እንጂ ኃላፊነት እንደሚሰማው ዜጋ ግዴታቸውን ሳይወጡ /ሳንወጣ በሀገር ጉዳይ ላይ የምንሰጠው አስተያየት ልክነት የጎደለው ከመሆን ባለፈ፤ በሞራል መመዘኛም ቀልሎ የሚታይ ፤ መታረም የሚገባው ከትናንት ይዘነው የመጣነውና ዛሬን እየሸፈነብን ያለ ችግር ነው።

ግብር መክፈል ከዚህም ባለፈ የስልጡንነትና የዘመናዊነት መገለጫ ጭምር ነው፡፡ ግብር ለምን እንደሚሰበሰብ በአግባቡ ማወቅና ለአላማው ተገዥ መሆን ዘመንን የመዋጀን ያህል የሚታሰብ አስተሳሰብ ልዕልና ነው። ይህንን እውነታ በህብረተሰቡ ውስጥ በአግባቡ በማስረጽ ጠንካራ ባህል አድርጎ ለማስቀጠል ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት ወሳኝ ነው ።

በአመት አንድ ጊዜ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን መፍጠር ሙብቱን በሚገባ ተረድቶ ግዴታው ላይ የተዘናጋውን ግብር ከፋይ ማህበረሰብ ወደ ትክክለኛው መንገድ ይመልሰዋል ተብሎ አይታመንም፡፡ የግብር ጉዳይ እንደኛ ባሉ ሀገሮች በትውልዶች ውስጥ እንዲሰርጽ በሀገራዊ የትምህርት ስርዓት ውስጥ ሊካተት የሚገባ አጀንዳ ሊሆን ይገባል።

ስለመሰረተ ልማት፣ ስለመብራትና ውሃ፣ ስለሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያና መንገድ፤ ስለሌሎችም ማህበራዊ አገልግሎቶች ጥያቄ እናነሳለን። ጥያቄ ማንሳታችን ተገቢ ነው። ጥያቄ ያነሳነው ግዴታችንን ተወጥተን ነው ወይስ ሳንወጣ? የሚለው ነውና ጉዳዩ በቀላሉ ሊታይ የሚገባው አይደለም።

ሀገር ሳንሰጣት የምትሰጠን ነገር የላትም፡፡ ከትላንት እስከዛሬ እየተቀበልን ያለነው የሰጠነውን ነው፡፡ ዛሬ ላይ የምንከፍለው ግብር ነገ ላይ መንገድና መብራት፣ ሆስፒታልና ንጹህ ውሃ ሆኖ ደጃችን የሚመጣ ነው፡፡ ለሀገር መስጠት ለራስ መስጠት ነው፤ ከዚህ የራቀ ሌላ ትርጉም የለውም፡፡

በሰለጠነው ዓለም የሰለጠነው ማህበረሰብ ግብርን ሲከፍል ደስ እያለው ነው። ምክንያቱም እንደ ዜጋ ከመንግስት የሚፈልጋቸው ማናቸውም ነገሮች ግብር ከፋዩ በከፈለው ገንዘብ የሚሰሩ በመሆናቸው ነው፡፡ እጃችንን ለመስጠት ሸሽገን፣ አገልግሎት ላገኘንበት ነገር ወደኋላ እያልን መንግስትን ማማረሩ ተገቢ አይደለም፡፡

መንግስትን ልንጠይቀው የምንችለው፤ ወይም ተጠያቂ ልናደርገው የሚገባን ግዴታችንን እስከ ተወጣን ድረስ ብቻ ነው፡፡ ያም ማለት እኛ በታማኝነት ግብር እየከፈልን መንግስት በታማኝነት የማያገለግለን ከሆነ ያኔ መንግስትን የመጠየቅ ያልተገደበ መብት አለን፡፡

ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ግብር ሳንከፍልና የግብር ማጭበርበር ተግባር እየፈጸምን ሀገር አልተለወጠችም፣ መንግስት እየሰራ አይደለም . . . ማለቱ መሰረት የሌለው ክስ ነው፡፡ ሀገርን ማገልገል ራስን ማገልገል ነው፡፡ ለሀገር መስጠት ለትውልዱ መስጠት ነው፡፡ ይህ ለሁሉም፣ በተለይም ለግብር ከፋዩ የኅብረተሰብ ክፍል ግልፅ መሆን አለበት።

ይህን እውነት ይዘው ነው የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆኔፍ ኬኔዲ "ሀገሬ ለእኔ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩላት" ሲሉ በምድረ አሜሪካ ሕዝባዊ ንቅናቄ የጀመሩት፡፡ ያ ንቅናቄ ነው የዛሬዋን አሜሪካ የፈጠራት፡፡

እኛም እንደ ሀገር፣ እንደ ማኅበረሰብ ለመቀጠልና ለመጠቀም "እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩ?" በማለት ራሳችንን መጠየቅ አለብን። ይህ አንዱና ወደ ለውጥ የሚመራን አቅጣጫ ነው፡፡ ይሄ አቅጣጫና ንቅናቄ ደግሞ እንደ ግብር መክፈል ትንሽ ከሚመስሉ፣ ግን ደግሞ የእድገትና የለውጥ የጀርባ አጥንት ከሆኑ ነገሮች የሚጀምር ነው፡፡

እንደ ዜጋ ለሀገራችን የሚጠበቅብንን ካላደረግን የምንፈልገው እድገትና ለውጥ አይመጣም፡፡ ሀገራዊ ለውጥ ያለው ግለሰባዊና ማህበራዊ ለውጥ ውስጥ ነው፡፡ ያ ለውጥ ደግሞ ሀገር ከመውደድና ለሀገር ከመቆርቆር የሚጀምር ነው፡፡

ያ ለውጥ ግብርን በወቅቱ ከመክፈልና ያገለገለችንን ሀገር መልሰን ስናገለግላት ነው፡፡ ራሳችንን ብቻ አፍቅረን፣ አመት በመጣ ቁጥር የሚጠበቅብንን ግብር ሳንከፍል ሀገር ወዳድ ነን ማለት አንችልም፡፡ የሀገር ፍቅር በወሬ ሳይሆን በተግባር የሚገለጽ ነው፡፡ በንቃትና በተሳትፎ የሚረጋገጥ ነው፡፡

ለሀገራችን እስካልነቃንና እስካልበቃን፣ እስካልሰጠንና ግዴታችንን እስካልተወጣን ድረስ ሕዝብ መንግስትን መንግስትም ሕዝብን ከመውቀስና ከመወቃቀስ አንድንም፡፡ እውቀት መር የሆነ ማህበራዊ ንቅናቄ ያስፈልገናል፡፡ ያም ግብር ለሀገር እድገትና ብልጽግና ዋነኛው መሳሪያ መሆኑን መገንዘብና ማስገንዘብ ነው፡፡

ሀገራችን በፖለቲካውም ሆነ በየትኛውም እንቅስቃሴ ውስጥ ገብቶት ሀገር የሚመራ፣ ገብቶት ዜጋ የሆነ ሕዝብና መንግስት ያስፈልጋታል፡፡ ግብር ስንጠየቅ ውሸትና ማጭበርበርን የምናስቀድመው ንፍገትን ከስግብግቦች ወርሰን ነው፡፡

በሀገር ጉዳይ ላይ የገባው ዜጋ ግብር ለመክፈል አያንገራግርም፡፡ ወይም ደግሞ ክፈል እስኪባል፤ ወይም ተገዶና ተከሶ ግብር እስኪከፍል አይጠብቅም፡፡ ለእንዲህ አይነቱ ትላንት ለነበረ፣ ዛሬም ላለ፣ ነገም ስላለመቀጠሉ ማረጋገጫ ከሌለው ሀገራዊ ችግር እራሳችንን ማራቅ አለብን፡፡

ግብር መክፈልን ግዴታችን ብናደርግና ንቁ ግብር ከፋይ ማኅበረሰብ ብንሆን፣ የልማት ስራዎቻችን ከዚህ ከፍ ባለ ደረጃ ላይ በደረሱ ነበር። ይህ ግን ሊሆን አልቻለም፤ ለዚህ ደግሞ የግብር አከፋፈል የተበላሸ ባህላችን ተጠያቂ ነው።

ግብር ሀገርና ሕዝብ ትውልድም የተሳሰሩበት፣ የተጋመዱበትና አንዱ ያላንዱ ህልውና የማያገኙበት ነው፡፡ እኛ በምንከፍለው ግብር ነገ ላይ እኛና የእኛ ልጆች እንደሚጠቀሙበት፤ የሀገር እድገት፣ የማኅበረሰብ ለውጥ በእኛ በታማኝነት ግብር መክፈል ውስጥ የተቀመጠ የመሆኑ ተጠየቅ ነው፡፡

ሰው ለሀገሩ ለመስጠት ከሳሳ እዛ ጋ ነው ትልቁ ድህነትና ኋላ ቀርነት ያለው፡፡ ሀገር በክብር፣ በልዕልና እያኖረችን ለሀገር መሰሰት ማለት የነውሮች ሁሉ ነውር፤ የነውር ጥግ ነው፡፡ ለሀገር መስጠት ለራስ መስጠትና ለሚመጣው ትውልድ መልካም ነገርን ማቆየት ነው፡፡

ለሀገር መስጠት ሀገራችን ለዋለችልን ውለታ የማይመጥናትን ትንሽ ነገር ማድረግ ነው፡፡ የእኛ ልጆች ነገ ላይ በመልካም ሀገርና በመልካም ማኅበረሰብ ውስጥ እንዲኖሩ ዛሬ ላይ ካለን ላይ ቆርሰን፣ ከሰራነው ላይ ገምሰን ለሀገራችን ልንሰጥ ይገባል፡፡

ደስ እያለን በኃላፊነት መንፈስ የሚጠበቅብንን ግብር መክፈል ባህላችን ልናደርገው ይገባል፡፡ ቀደም ሲል እንደሰማነው፣ አዲስ አበባ ውስጥ ካሉ በርካታ ግብር ከፋዮች ውስጥ 300 ብቻ የሚሆኑት ናቸው ግዴታቸውን አውቀው ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ያሉት፡፡ ሌሎቻችንስ፣ ለሀገራችን ታማኝና ብቁ መሆን ለምን አቃተን?

እንደ ሀገር የግብር ከፋዮችን አሃዝ ስናየው ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ አብዛኞቹ በሚባል ደረጃ ተገደውና ተለምነው የሚከፍሉ ናቸው፡፡ በአንድ ሀገር ላይ የማኅበረሰቡ የግብር መክፈል ንቃት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ግዴታ ብቻ ሳይሆን ደስ ብሎን ግብር መክፈልን ልማድ እስካላደረግን ድረስ ከድህነት እና ከኋላቀርነት የምንወጣበት መንገድ እያራቅነው የመሄዱ እውነታ ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም፡፡

እንደሀገር የራቁብን የስኬት መንገዶች፣ ያልተከፈቱልን የሰላም በሮች ይህን ከመሰለውና ግዴታን ካለማወቅ በሚመነጩ አጉል ልማዶች የመነጩ ናቸው፡፡ ስልጣኔ መብትን መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ግዴታንም ማወቅ ነው፡፡ በአንዱ ውስጥ አንዱን አጉድሎ ስልጣኔ የለም፡፡ መብትና ግዴታ መሳ ለመሳ ሲሄዱ ነው ሀገር ሰለጠነች፣ ማኅበረሰብ ዘመነ የሚባለው፡፡

**ግብር መክፈል ከዚህም ባለፈ የስልጡንነትና የዘመናዊነት መገለጫ ጭምር ነው፡፡ ግብር ለምን እንደሚሰበሰብ በአግባቡ ማወቅና ለአላማው ተገዥ መሆን ዘመንን የመዋጀን ያህል የሚታሰብ አስተሳሰብ ልዕልና ነው። ይህንን እውነታ በህብረተሰቡ ውስጥ በአግባቡ በማስረጽ ጠንካራ ባህል አድርጎ ለማስቀጠል ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት ወሳኝ ነው።**

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የበልግ ወቅት ግብርናውን በተቀናጀ አግባብ

**ስምስም መንግሥቱ**



ሀገሪቱ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት መስራቷን ተያይዛዋለች። ለእዚህም በእያንዳንዱ የግብርና ወቅት ላይ መሰረት ተደርጎ እየተሰራ ነው። ዘንድሮም በመኸር እርሻ ስራ ላይ ርብርብ ሲደረግ ቆይቶ አዝመራ በመሰብሰብ ስራው ተጠናቋል። አሁን ደግሞ በበልግ ወቅት የግብርና ስራ ላይ ርብርብ እየተደረገ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት የተቀናጀ ስራ የሚካሄድበት ተግባር ሆኗል። በአሁኑ ወቅትም የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት አዝመራ እየተሰበሰበ ይገኛል።

የግብርናውን ዘርፍ የሚመራው አካልም አስፈላጊውን ግብዓት፣ ቴክኖሎጂና የመሳሰለውን ማቅረብን ጨምሮ ሥራውንም በመከታተል እያደረገ ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ ቀጥሏል። ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ እንደ ሀገር በዘርፉ የተያዘውን እቅድ ለማሳካት እንዲህ ያለው የልማት ቁርጠኝነት፣ ተነሳሽነት፣ ክትትልና ድጋፍ ፋይዳው ከፍተኛ ነው።

አሁን ወቅቱ የበልግ ነው። ለእዚህ የሚያስፈልገው ዝናብ ተገኝቷል። የግብርናውን ዘርፍ የሚመሩት አካላትም ፊታቸውን ወደ በልግ አብቃይ አካባቢዎች መልሰዋል። የግብርና ሥራው ዝናብን መሠረት ያደረገ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በተለይም የሚጥለውን ዝናብ እንዲሁም የጣለውን ዝናብ ተከትሎ የተፈጠረውን እርጥበት በጊዜው ለመጠቀም ዝግጁ ሆኖ መጠበቅ ግድ ይላል። እኛም ከዝግጅት ምእራፍ ጀምሮ በበልግ የግብርና ሥራ ላይ እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ ቃኝተናል።

እንደ ሀገር በበልግ የግብርና ሥራ ትልቅ ሽፋን ካላቸው የኢትዮጵያ ክፍሎች አንዱ የአማራ ክልል ሲሆን፣ በክልሉ በበልግ ከፍተኛውን ሽፋን የሚይዙት አካባቢዎች ደግሞ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ጎንደር፣ የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞኖች ናቸው።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ቃልኪዳን ሽፈራው በክልሉ የበልግ ዝናብን በወቅቱ ለመጠቀም እየተደረገ ስላለው እንቅስቃሴ ሲገልፁ፤ ቀደም ባሉት የበልግ ወቅቶች ከፍተኛ የሆነ የዝናብ መቆራረጥ ይከሰት እንደነበር አስታውሰው፤ ይህም በግብርና ሥራው ላይ ተግዳሮት መሆኑን ተከትሎ ተደጋጋሚ ጉዳት የተስተናገደባቸው ጊዜያቶች እንደነበሩ ይናገራሉ።

እንዲህ ያሉ ችግሮች እንዳያጋጥሙ በዚህ የበልግ ወቅት የተገኘውን ዝናብ በወቅቱ በአግባቡ ለመጠቀም የቅድመ ዝግጅት ሥራው የተጠናከረ መሆኑን ይጠቁማሉ። የሚያጋጥመውን የዝናብ መቆራረጥ ችግር ለመፍታት የውሃ አማራጮች የሆኑ እድሎችን ሁሉ ለመጠቀም ጥረት እንደሚደረግም ገልጸዋል።

እንደ አቶ ቃልኪዳን ገለጻ፤ በክልሉ በዚህ የበልግ የግብርና ሥራ በተያዘው ቅድመ እቅድ ወደ 218 ሺ ሄክታር መሬት በተለያየ ሰብል ይሸፈናል፤ ከዚህም አራት ሚሊየን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብም በእቅዱ ተካትቷል። በእስካሁኑ እንቅስቃሴም ወደ 123ሺ ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል። ከዚህ ውስጥም ትልቁን የዘር ሽፋን የያዙት ገብስና ስንዴ ሰብሎች ሲሆኑ፣ 54ሺ ሄክታር መሬት በገብስ፣ 23ሺ ሄክታር መሬት ደግሞ በስንዴ ሰብሎች ተሸፍኗል። ቀሪው መሬት ደግሞ በትንሽ እርጥበት ምርት በሚሰጡ ሰብሎች እንዲሸፈን ይደረጋል። በዚህ የበልግ ወቅት ሰሜን ሸዋና ደቡብ ወሎ ዞኖች በመሬት ስፋት ሰፋ ያለ ሽፋን አላቸው። በአጠቃላይ በበልግ የግብርና ሥራ የታቀደውን መሬት በዘር ለመሸፈን እንቅስቃሴው ተጠናክሯል።

እስካሁን ባለው እንቅስቃሴ የቅድመ ዝግጅት ሥራውና የሚጠበቀው የዝናብ ወቅት የተጣጣመ አይደለም። የዝናብ ስርጭቱም ሁሉንም የበልግ አብቃይ አካባቢዎች የሸፈነ አይደለም። በዚህ ረገድም ሰሜን ወሎና ደቡብ ወሎ የተወሰኑ አካባቢዎች ይጠቀሳሉ። ዝናብ የጣለባቸው አካባቢዎችም ቢሆኑ ወደ ዘር ሥራ ከገቡ በኋላ ዝናቡ መቆራረጥ እያሳየ ነው። በቀሪው ጊዜ መሻሻል እንደሚኖር ይጠበቃል። ቀድሞ በጣለው ዝናብ እርጥበት የያዘውን መሬት በማረስ የተሻለ ምርት የሚሰጡ ሰብሎች እንዲዘሩ በማድረግ እቅዱን ለማሳካት ጥረት እየተደረገ ነው።

ክልሉ የእስካሁኑን የበልግ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ገምግሟል። ይህንኑ በተመለከተም አቶ ቃልኪዳን እንዳስረዱት፤ የበልጉ የዝናብ ወቅት ገና በመሆኑ ከዝናብ አኳያ ተስፋ ስላለው የተጀመረውን እንቅስቃሴ አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ ነው አቅጣጫ የተቀመጠው። ከዚህ አንጻርም በጣለው ዝናብ የተያዘውን እርጥበት ጥቅም ላይ በማዋል፣ ዝናቡ ሲጥል ደግሞ ፈጥኖ ወደ ሥራ ለመግባት ዝግጁ መሆን ከአርሶ አደሩም ሆነ ልማቱን በተለያየ መንገድ ከሚደግፉ አካላት የሚጠበቁ ተግባራት ናቸው። ከግብዓት ጋር በተያያዘም በተለይም አርሶ አደሩ የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) እንዲጠቀም እየተበረታታ ነው። ጎን ለጎንም ማዳበሪያ፣ የተሻሻለ ምርጥ ዘርና አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን ለማሟላት ጥረት እየተደረገ ነው።

ባለፉት ጥቂት የምርት ወቅቶች በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በነበረው ጦርነት ጋር በተያያዘ የግብርና ስራዎች ተስተጓጉለው እንደነበር ይታወሳል። አሁን ሰላም በመስፈኑ በጦርነት ቀጠና ውስጥ ሆነው የግብርና ልማቱ በተስተጓጎለባቸው አካባቢዎች ላይ የተለየ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ስለመሆኑ አቶ ቃልኪዳን ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ ‹‹ዝናብ በሚጥልባቸው አካባቢዎች ሁሉ ልማቱ ይከናወናል። በጦርነት ቀጣና ውስጥ የነበረው ሰሜን ጎንደር አካባቢ እስከ ባለፈው ሳምንት ድረስ ዝናብ ባለመጣሉ በቀጣይ በሚጠበቀው ዝናብ ልማቱን ለማከናወን ዝግጅት ተደርጓል›› ብለዋል።

በዚህ የበልግ ወቅት የግብርና ሜካናይዜሽን ከመጠቀም አኳያ ስላለው እንቅስቃሴም በተመለከተ በመኸሩም ሆነ በበልጉ ሰፋፊ የእርሻ መሬት ባላቸው አካባቢዎች መሬቱን ለማረስ ትራክተር የመጠቀም ሁኔታ መኖሩን አስታውቀዋል። ከዚህ የበልግ ወቅት ጎን ለጎን እየተከናወነ ባለው የበጋ መስኖ ልማት የደረሰው ሰብል እየተሰበሰበ መሆኑን ጠቅሰው፣ በዚህም የስንዴ ልማቱ ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዝ ተናግረዋል። በአጠቃላይ በመስኖ ልማቱ የተሻለ ውጤት መኖሩን ጠቁመዋል። ለሁለተኛ የመስኖ ልማት ዝግጁ የሆኑ አካባቢዎች መኖራቸውንም ገልጸዋል።

ሌላው በልግ አብቃይ የሆነው የደቡብ ክልልም በተመሳሳይ ወቅታዊ ከሆነው የበልግ የግብርና እንቅስቃሴን በተመለከተ ግምገማ አካሂዷል። የግምገማውን የትኩረት አቅጣጫና እየተከናወኑ ስላሉ ተግባራት ያነጋገርናቸው የደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊና የእርሻ ዘርፍ ኃላፊን አቶ አድማሱ አወቀ እንዳሉት፤ የግምገማው አንዱ አላማ ንቅናቄ መፍጠር ነው። ንቅናቄ መፍጠር ያስፈለገው ባለፉት የበልግ ወቅቶች በከፍተኛ ሁኔታ አጋጥሞ በነበረው የዝናብ መቆራረጥ በበልጉ ብቻ ሳይሆን በመኸሩም ጊዜ በሰብል ልማቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶ ስለነበር ነው። ይህንን ታሳቢ በማድረግ አሁን ላይ የሚፈጠረውን መልካም አጋጣሚ ጥቅም ላይ በማዋል ያለፈውን ለማካካስ በንቅናቄ እንዲሰራም ነው።

ውጤታማ የሆነ አፈጻጸም ለማስመዝገብም የቴክኖሎጂ አጠቃቀም በማሻሻል ላይ ትኩረት እንዲሰጥ እንዲሁም የሚስተዋሉ የምርታማነት ማነቆዎችን ለመፍታት፣ በነዚህ አቅጣጫዎች ላይ ቀድሞ ተነጋግሮ ወደ ሥራ በመግባት የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት ጭምር ነው የግምገማ መድረኩ የተካሄደው ሲሉም ያብራራሉ። የበልግ ዝናብ መቆራረጥም ሆነ የመብዛት ሁኔታ ስለሚያጋጥም ይህንን ሁሉ ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ ዝግጅት መደረጉን ይገልጻሉ።

የልማቱ ሥራ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ ገብቶ እንዲከናወን፣ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ሥራ እየተሰራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ አድማሱ፤ የግብርና ሥራው ከዝናብ ጥገኝነት የተላቀቀ እንዲሆን ለማስቻል በማሳ ውስጥ የዝናብ ውሃ ለመያዝ እንዲቻል እንዲሁም እርጥበት ለማቆየት የሚያስችል የተለያየ የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት ግብረ ኃይሉ መዋቀሩን አስረድተዋል። የሚያጋጥመውን የውሃ ችግር ለመፍታት ብቻ ሳይሆን፣ ከፍተኛ ውሃ ሲኖር ውሃውን ወደ ውጭ የማስወጣት ሥራዎችንም ታሳቢ ያደረገ መሆኑን አመልክተዋል። በሂደት ያጋጥማሉ ተብለው በተለዩ ጉዳዮች ላይም መድረኩ እንደተነጋገሩበት ገልጸዋል።

የግብዓት አቅርቦትን በተመለከተም አቶ አድማሱ እንደገለጹት፤ በአካባቢው ባለፉት ጊዜያቶች አጋጥሞ የነበረው የዝናብ እጥረት በምርጥ ዘር አቅርቦት ላይም የራሱን ተጽእኖ ያሳደረ በመሆኑ በዚህ ረገድ ያለውን ችግርና በተለያየ ምክንያት ሊነሳ የሚችል ወረርሽኝንም ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚያስችል መልኩ ዝግጅት ተደርጓል። በተለይም የምርጥ ዘር አቅርቦቱን ከአርሶ አደሩም በመፈለግ ጭምር ክፍተቱን ለመሙላት ጥረት ይደረጋል።

የአፈር ማዳበሪያ እስከ ሰባት መቶ ሺ ኩንታል ያስፈልጋል። ግብዓቱ ወደ ክልሉ እየገባ ሲሆን፣ እስካሁንም ከሶስት መቶ ሺ ኩንታል በላይ ገብቷል። በዚህ ረገድ ያለውን ክፍተት ከወዲሁ ለመግለጽ ባይቻልም እጥረት ይኖራል የሚል ስጋት ግን አለ።

እንደ አቶ አድማሱ ገለጻ፤ በበልግ የግብርና ሥራ አንድ ሚሊዮን 44ሺ 888 ሄክታር መሬት ለማረስ የታቀደ ሲሆን፣ መሬቱንም እንሰትን ጨምሮ ወደ 13 በሚሆኑ የሰብል አይነቶች ለመሸፈን ታቅዷል። ከነዚህ ውስጥም በስፋት የሚጠበቁት የሰብል ምርቶች በቆሎ እና ማሽላ ሲሆኑ፤ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትም ይከናወናል። በአጠቃላይ ከሚለማው መሬት ወደ 102ሚሊዮን 489ሺ 692 ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዷል። እቅዱን ለማሳካት ከንቅናቄ ሥራ ጀምሮ ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም ወደ ተጠናከረ ሥራ አልተገባም።

የዝናብ ስርጭቱ አሁን ባለው ሁኔታ ጥሩ የሚባል እንደሆነም ጠቅሰው፣ ክልሉ ሁሉም አካባቢ በልግ አብቃይ እንደሆነ፣ ለልማቱም ዝግጁ እንደሆኑና አርሶ አደሩን በተለያየ መልኩ የሚያግዙ ባለሙያዎችም ዝግጁ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ከግብዓት አቅርቦት ዝግጅት አኳያም ለ2015/2016 የምርት ዘመን የማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሞ ወደብ ላይ ከደረሰው አጠቃላይ ማዳበሪያ ውስጥ 90 በመቶው ማዕከላዊ መጋዘን መድረሱን የግብርና ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ ሰሞኑን መግለጻቸው ይታወሳል። እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ መንግሥት ለማዳበሪያ ግዥ 21 ቢሊዮን ብር ድጎማ አድርጓል። ድጎማው አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ ሲሆን፣ በአማካይ በእያንዳንዱ የማዳበሪያ ኩንታል ዋጋ ላይ የ1 ሺህ 566 ብር ድጎማ ይሸፍናል።

ምርጥ ዘር አቅርቦትን በተመለከተም 370 ሺህ ኩንታል ምርጥ ዘር ከፌደራል ተቋማት እና የምርጥ ዘር አባዢዎችን በማቀናጀት ተደራሽ ይደረጋል ብለዋል። ጉድለቶቹን ለመሙላት የክልል ምርጥ ዘር አባዢዎችን እንጠቀማለን ሲሉም ተናግረዋል።

የግብርና ግብዓትን ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ባለፉት ጥቂት አመታት በኮቪድ- 19 ቫይረስ ወረርሽኝ እና በሩሲያና ዩክሬን መካከል በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት የግብርና ግብዓት ተደራሽነት ላይ ይስተዋል የነበረውን ችግር በመፍታት የምርጥ ዘርና የግብርና ግብዓቶቹን በወቅቱ ተደራሽ በማድረግ የግብርናውን ዘርፍ ለማሳደግ በትኩረት እየተሰራ እንደሆነም ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

በዚህ የበልግ ወቅት ለመሸፈን በእቅድ ስለተያዘው መሬትና ስለሚጠበቀው የምርት መጠን ደግሞ በግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ከበደ ላቀውን ጠይቀናቸው በሰጡት ምላሽ፤ ‹‹2 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በበልግ ለመሸፈን ታቅዷል። ከዚህም ወደ አራት ሚሊየን ኩንታል የሰብል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዷል። እስካሁን በተከናወነው የግብርና ሥራም ከግማሽ በላይ የሚሆነው መሬት ታርሷል።

በበልግ የግብርና ወቅት በስፋት የሚለሙት በቆሎ፣ ማሽላና ስንዴ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ከሚሸፈነው መሬት አብዛኛው አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች ማሳ መሆን ተናግረዋል። ቀሪው ላይ የሚከናወነው ደግሞ ለሀገራዊ ምርት ድርሻ ይኖረዋል ተብሎ የሚጠበቅ መሆኑን ጠቁመዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# አዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ለቴክኒክና ሙያ እድገት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

በስራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢኒስቲትዩት እንዲሁም የአካዳሚክ ጉዳዮች ኃላፊ ዶክተር ገነነ አበበ አዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት ብዙ አማራጮችን ይዞ እንደመጣ ይናገራሉ። አንዱ በዚህ ፖሊሲ እንደተቀመጠው ከታችኛው ክፍል ጀምሮ ማለትም በአጠቃላይ ትምህርት ጭምር እንዲካተት መደረጉ ሲሆን ይህ ደግሞ ሙያንም ሆነ ትምህርቱን ተወዳጅ ለማድረግ ያስችላል። በቴክኒክና ሙያ ዙሪያ ያለውን አመለካከትም ይለውጣል። ተማሪዎች ሙያ ወዳድ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

ሌላው ፖሊሲው የፈጠረው እድል ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲ ገብተው በሚማሩበት ደረጃ ልክ በቴክኒክና ሙያም ገብተው እንዲማሩ ማስቻሉ ነው። እስከ ዶክትሬት ዲግሪ ድረስ መማር እንደሚችሉ ግንዛቤ የሚፈጥርና የሚገፋፋቸው ሆኗል። ቴክኒክና ሙያ በባህሪው ሥራ ተኮር ትምህርት በመሆኑ በሙያ ተመርቀው ኢኮኖሚውን ለማሳደግ የሚደረግ ትምህርት ይሰጥበታልና አሁን በተፈጠረው እድል ብዙዎች እንደሚገቡ ይታመናል ይላሉ።

አዲሱ ፖሊሲ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት የጀርባ አጥንት የሆነው የኢንዱስትሪ ተሳትፎን ከማሳለጥ አኳያ ብዙ እድሎችን ይዞ መጥቷል። አንዱ ከዚህ በፊት የነበረውን የኢንዱስትሪዎች ትስስርን በእጅጉ የሚያጠናክርበትና የሚያሰራ ነው። ኢንዱስትሪዎች እንዴት ማሳተፍ ብሎም ትርፋማ ማድረግ እንደሚቻል ያመላክታል።

የቴክኒክና ሙያ ትምህርት በማህበረሰቡ ዘንድ ዝቅተኛ አመለካከት እንዲሰጠው ያደረገው አሰራሩና ፖሊሲ ነበር፤ በአዲሱ ፖሊሲ ይህ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል። ከዚህ በፊት እስከ ደረጃ አምስት ብቻ የነበረው ሁኔታ ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲን ብቻ እንዲመለከቱና እንዲመርጡት አድርጓቸው ቆይቷል። አሁን ግን በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ እስከ ሦስተኛ ዲግሪ መድረስ የሚቻልበት በመሆኑ ብዙዎች ምርጫቸው ያደርጉታል።

አሁን በወጣው ፖሊሲ አንድ የ12ኛ ክፍል ተማሪ የከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ነጥብ ካገኘ ቴክኒክና ሙያ ውስጥ ገብቶ የመጀመሪያ ዲግሪውን መከታተል ይችላል። ይህ ደግሞ ልክ እንደ ዩኒቨርሲቲዎች ሁሉ አራት ዓመታትን በትምህርት በማሳለፍ ነው የሚገኘው ያሉት ዶክተር ገነነ፤ በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ትምህርት የሚጠናቀቀው 12ኛ ክፍል በመሆኑ እንደዚህ ቀደሙ የ10ኛ ክፍል ተማሪ የሆነ ወደ ቴክኒክና ሙያ አይገባም ማለት ነው። ይህ ደግሞ የሙያን ጥቅም በአግባቡ ተረድቶ ለትምህርቱ ዝግጁ ሆኖ የሚገቡ ተማሪዎችን እንደሚያበራክትም ይናገራሉ።

ዶክተር ገነነ፤ በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ መማር ከዚህ በኋላ የምርጫ ጉዳይ እንጂ የውጤት ጉዳይ አይሆንም። ምክንያቱም ቴክኒክና ሙያ ከፍተኛ ተቋም የመግባት ሁኔታው ተመሳሳይነት ያላቸው እድሎችን ይዟል። ከደረጃ ስድስት በላይ ያሉ ትምህርቶችን የሚማሩ ተማሪዎች ልክ እንደከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ ዓመቱን ጠብቀው ይመረቃሉ። ደረጃ አምስትን ጨምሮ ያሉት ግን እንደተማሪው አቅምና ፍጥነት ይወሰናሉ። ቴክኒክና ሙያ ላይ ዋጋ የሚሰጠው ዓመታት ማስቆጠሩ ሳይሆን ብቁ ሆኖ መውጣቱ ነውና በትንሽ ጊዜ በጣም ሙያዊ ብቃታቸውን እያሳዩ ከመጡ ደረጃውን መሻገርና የብቃት ምዘና ወስደው ወደ ሥራ መሰማራት እንደሚችሉ ያስረዳሉ።

በአዲሱ ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት ከቴክኒክና ሙያ የሚወጡ ተማሪዎች በሁለት አይነት መልኩ እንዲሰሩ ተደርገው ይመረቃሉ። የመጀመሪያው በራሳቸው ሥራ እንዲፈጥሩ ሲሆን፤ ሁለተኛው ተቀጥረው እንዲሰሩ ነው። ለዚህ ደግሞ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥሯል። አንዱ ገበያው የሚፈልገውን እያዩ ማሰልጠን ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ከኢንዱስትሪዎች ጋር ማስተሳሰር ነው። አሁን አካሄዱ ከውስጥ ወደ ውጭ የሚል ነው፤ ከራሳችን ተነስተን ነገሮችን እያሰፋን ገበያውን እንይዛለን። በዚህም የአቅርቦትና ፍላጎት ልዩነት እንዳይኖር አምስት ዋና ዋና የሥራ ዘርፎችን እናሰለጥናለን። በግብርና፣ ሆቴልና ቱሪዝም፣ ማዕድን ቁፋሮ(ማይኒንግ)፣ ማንፋክቸሪንግና አይሲቲ የተማሪዎቻችን የሥራ ምንጮች ይሆናሉም ይላሉ።

ተቋማት ስልጠና ሲሰጡ ከአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት ጋር በተዛመደ መልኩ እንዲሰጡ መደረጉም ሌላው አዲሱ ፖሊሲ ያመጣው መልካም እድል በመሆኑ እንደ ዩኒቨርሲቲዎች ሁሉ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችም እንደ አካባቢያቸው የተፈጥሮ ሀብት ተለይተው ትምህርት የሚሰጡ ይሆናልና አካባቢያቸውን ለይተው የተመረጡትን ዘርፎች ብቻ አይተው በቀላሉ መስራት እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። እድሉ ደግሞ ለተማሪው ብቻ ሳይሆን ለኢንዱስትሪውም ነው።

ታዲያ ይህ ሁሉ ምቹ ሁኔታ ለዘንድሮ የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ምን አማራጭ ይዞ መጥቷል ከተባለ አንዱ ከ50 በታች ያመጡ 100 ሺ ተማሪዎች የማካካሻ ትምህርት እንዲወስዱ በየዩኒቨርሲቲው የተመደቡ ቢሆንም አንፈልግም ካሉና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትን ከመረጡ እድሉ የሚሰጣቸው መሆኑ ነው። ሌላው ከ50 በላይ ያመጡትም ቢሆኑ እድሎቹ እንዳላቸው ያመላከተ ነው። ከዚያም ባሻገር እንዳለፉት ጊዜያት ውጤት ያልመጣላቸውም በተቀመጠላቸው ውጤት መሰረት የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እድል ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

በቅርቡ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ፤ በ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል 608 ሺ 666ቱ ወደ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ገብተው እንደሚሰለጥኑ ይደረጋል። በሀገር አቀፍ ደረጃ በ2015 ዓ.ም ወደ ማሰልጠኛ ተቋማት ሊገቡ የሚችሉ ሰልጣኞች ቁጥር 760 ሺህ 832 ሲሆን፤ 20 በመቶ የሚሆኑት ከቴክኒክና ሙያ ውጭ ባሉ ማሰልጠኛ ተቋማት ይገባሉ። በመሆኑም በሀገር አቀፍ ደረጃ ቴክኒክና ሙያ የሚገቡት ሰልጣኞች ቁጥር ሰፋት ያለው ይሆናል።

በ2015 ዓ.ም የመቁረጫ ነጥብ የሰልጣኞች ድልድል የኢንዱስትሪውን የሰው ኃይል አሰላለፍ መሰረት በማድረግ የተሰላ በመሆኑ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የስራ ገበያውን፣ የሰው ኃይል ፍላጎትና የአካባቢውን የልማት ቀጠና መሰረት በማድረግ ቅበላ ያደርጋሉ። መቁረጫ ነጥቡ የ2014 ዓ.ም 12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተናን የወሰዱ ተማሪዎችን ታሳቢ ተደርጎ የተሰራ በመሆኑ ለ2015 ዓ.ም ብቻም ያገለግላል። በ2013 ዓ.ም እና በ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና ወስደው በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓት ያልገቡ ተማሪዎች ደግሞ የሚስተናገዱት በ2014 ዓ.ም በነበረው የመቁረጫ ነጥብ መሰረት ይሆናል ብለዋል በመግለጫቸው።

እንደሚታወቀው ከዚህ ቀደም የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤት ታይቶ የቴክኒክና ሙያ እንዲገቡ ይደረጋል። አሁን ግን በአዲሱ ፖሊሲ 10ኛ ክፍል ላይ የሚሰጥ ፈተና ስለሌለ በ10ኛ ክፍል ውጤት መሰረት ወደ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የሚገባ አይኖርም። በዚህም በ2013 እና በ2014ዓ.ም የተማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚስተናገዱት በሁለት አይነት መንገድ ይሆናል። የመጀመሪያው ትምህርታቸውን 11ኛ ክፍል ገብተው መማር ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ አጫጭር ሥልጠና ወስደው የቴክኒክና ሙያን ይቀላቀላሉ። በተጠቀሰው ዓመት ውስጥ ያጠናቀቁ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ በተፈጥሮና ማህበራዊ ሳይንስ አጠናቀው የመቁረጫ ነጥቡን የሚያሟሉ ተማሪዎች በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ውስጥ በሚሰጡ ሁሉም ሙያዎች ላይ እኩል የመወዳደርና የመሰልጠን መብት እንዳላቸው ያብራራሉ።

የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን የማዘመን፣ ተደራሽ የማድረግና በትኩረት መስክ የማደራጀት ስራ እየተሰራ እንደሚገኝ ያነሱት ሚኒስትሯ፤ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱን ለስራ ገበያው በሁሉም ደረጃዎች የሠለጠነ የሰራተኛ ኃይልና ተስማሚ ቴክኖሎጂ የማቅረብን ተልእኮ ለቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የተሰጠ በመሆኑ ይህንን ከማስተግበር አኳያ ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል። ተልዕኮውን ውጤታማ ለማድረግም በእውቀቱ፣ በክህሎቱ፣ በአመለካከቱ ብቁ የሆነ ዜጋ ለማፍራት ከሰልጣኝ ቅበላ እስከ ስራ ማስተሳሰር ያሉ ሂደቶች ጥንቃቄን በሚሹ መልኩ የሚከናወንም ይሆናል።






በ2015 ስልጠና ዘመን የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት የመግቢያ ነጥብን በተመለከተ እንዳስቀመጡትም፤ በደረጃ አንድና ሁለት ስልጠና የሚሳተፉ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያና ቅድመ ዝግጅት (12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ) የተፈጥሮ ሳይንስ የመቁረጫ ነጥብ ለወንዶች 157 ሲሆን፤ ወንዶች ሆነው በታዳጊ ክልሎችና አርብቶ አደሮች አካባቢ ለሚኖሩ ተማሪዎች 156 ነው። ለሴቶች ደግሞ 156 የተወሰነ ሲሆን፤ ሴት ሆነው በታዳጊ ክልሎችንና አርብቶ አደሮች አካባቢ ለሚኖሩ መቁረጫ ነጥቡ በአንድ ነጥብ ዝቅ ተደርጎ 155 እንዲሆን ተወስኗል። ለሁሉም ክልል አካል ጉዳተኞች 130 ካመጡ ደረጃውን ያሟላሉና ትምህርቱን መከታተል ይችላሉ።

በማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ያሉ በደረጃ አንድና ሁለት ስልጠና የሚሳተፉ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያና ቅድመ ዝግጅት (12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ) ተማሪዎች የመቁረጫ ነጥብ ደግሞ ለወንዶች 148 ነው። ለታዳጊ ክልሎችና አርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚኖሩ ወንድ ተማሪዎች ደግሞ 142 ካመጡ ትምህርቱን መከታተል ይችላሉ። በተመሳሳይ ሴቶች 144 ማምጣት የሚጠበቅባቸው ሲሆን፤ ታዳጊ ክልሎችንና አርብቶ አደር አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች ደግሞ 141 ማምጣት ግዴታቸው ይሆናል። ለሁሉም ክልል አካል ጉዳተኞች 130 ካመጡ በቂ እንደሆነ በመግለጫው ተመላክቷል።

ደረጃ ሦስትና አራት ስልጠናን የሚወስዱ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያና ቅድመ ዝግጅትነ (12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ) በተፈጥሮ ሳይንስ የመቁረጫ ነጥባቸው ለወንዶች ከ158 እስከ 245 ሲሆን፤ በታዳጊ ክልሎችና አርብቶ አደር አካባቢ ለሚኖሩ ወንዶች ደግሞ 157 እስከ 202 ማምጣት ግድ ነው። ወደ ሴቶቹ ሲገባ 157 እስከ 217 ድረስ ማምጣት ይኖርባቸዋል። በታዳጊ ክልሎችንና አርብቶ አደሮች አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች ደግሞ 156 እስከ 201 ሲያመጡ ነው ደረጃውን የሚያሟሉትና ትምህርቱን መከታተል የሚችሉት ተብሏል። በዚህ ደረጃ ለሁሉም ክልል አካል ጉዳተኞች የተሰጠ የመቁረጫ ነጥብ ደግሞ ከ131 እስከ 148 ነው።

በማህበራዊ ሳይንስ ደረጃ ሦስትና አራት ስልጠናን የሚወስዱ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያና ቅድመ ዝግጅት (12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ) የመቁረጫ ነጥብ ደግሞ ለወንዶች ከ149 እስከ 202 ሲሆን፤ በታዳጊ ክልሎችና አርብቶ አደር አካባቢ ለሚኖሩ ወንዶች 143 እስከ 172 ሆኗል። ሴቶቹ ደግሞ 145 እስከ 178 ማምጣት ይኖርባቸዋል። በታዳጊ ክልሎችንና አርብቶ አደሮች አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች ደግሞ 142 እስከ 170 ነው ተብሏል። ለሁሉም ክልል አካል ጉዳተኞች ከ131 እስከ 148 ድረስ ካመጡ ትምህርቱን መከታተል እንደሚችሉ ተቀምጧል።

በተፈጥሮ ሳይንስ ደረጃ አምስትን የሚቀላቀሉ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያና ቅድመ ዝግጅት(12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ) ተማሪዎች ደግሞ ወንዶቹ 246 ያመጡ ሲሆኑ፤ ለታዳጊ ክልሎችና አርብቶ አደሮች አካባቢ ለሚኖሩ ወንዶች ደግሞ 203 ማምጣት ግዴታ እንደሆነ በመግለጫው ተነስቷል። በተመሳሳይ ለሴቶቹም የተቆረጠ ነጥብ አለ። ይህም 218 ማምጣት ነው። ታዳጊ ክልሎችንና አርብቶ አደሮች አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች ደግሞ 202 ማምጣት እንዳለባቸው ተወስኗል። ለሁሉም ክልል አካል ጉዳተኞች ደግሞ 149 ዝቅተኛ የመግቢያ ውጤታቸው እንደሆነ ተነግሯል።

ደረጃ አምስትን የሚቀላቀሉ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያና ቅድመ ዝግጅት(12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ) የማህበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች ደግሞ ወንዶቹ 203 ያመጡ ሲሆኑ፤ ለታዳጊ ክልሎችና አርብቶ አደሮች አካባቢ ለሚኖሩ ወንዶች 173 ማምጣት ግዴታ ነው። በዚህ ደረጃ የሚሰለጥኑ ሴቶች ደግሞ 179 ማምጣት ይኖርባቸዋል። በታዳጊ ክልሎችንና አርብቶ አደሮች አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች ማምጣት ያለባቸው ውጤት 171 ነው። ለሁሉም ክልል አካል ጉዳተኞች ደግሞ 149 ዝቅተኛ የመግቢያ ውጤታቸው ሆኗል።

የመቁረጫ ነጥቡ ይፋ እንደተደረገ በነጥቡ መሰረት ተቋማቱን ለመቀላቀል ዝግጅት ካደረጉ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች መካከል አንዱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲሆን፤ መጋቢት 1 ቀን 2015 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ስልጠና እንዲሁም ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮዎች በ2015 የትምህርት ዘመን ወደ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ለሚገቡ አዲስ ሰልጣኞች የተማሪ ቅበላ ማስጀመሪያ መርሃ ግብርን አዘጋጅተዋል። መርሃግብሩ የነበረው በእንጦጦ ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ ቅጥር ግቢ ውስጥ ነበር።

የተማሪ ቅበላ ማስጀመሪያ መርሃ-ግብሩ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ እንዳሉትም፤ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና በተጨባጭ ተግባር የታገዘ በቴክኒክ ትምህርት መሰልጠን ለሚፈልጉ እንዲሁም በተለያዩ የሙያ ዘርፎች አዳዲስ ክህሎቶችን ማዳበር ለሚሹ ሰዎች የሚሰጥ የፈጠራ ክህሎትን ለማስተማር የሚያስችል ተመራጭ የትምህርት ዘርፍ ነው። ተማሪዎች በሚፈልጉት የሙያ ዘርፍ እና ደረጃ ላይ መማር የሚችሉበት እድል ስለሚሰጣቸውም ሊጠቀሙበት ይገባል።

በመርሀ ግብሩ የታደሙት የቴክኒክና ሙያ ስልጠና እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሀቢባ ሲራጅ በበኩላቸው፤ ዘንድሮ ወደ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ለሚገቡ ተማሪዎች የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ሙሉ ዝግጅት አድርገዋል። ከዚህ በተጨማሪም 108 የሙያ አይነቶች በስምንት ኮሌጆች ስልጠና ይሰጣል ሲሉ አብስረዋል። እናም እነዚህን ለመጠቀም ተማሪዎች ከምንጊዜውም በተሻለ መልኩ ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል በማለት ለዛሬ የያዝነውን ሀሳብ ቋጨን።

# "ፈተና ቢኖርም ፈተናውን ተጋፍጠን አርሶ አደሮቻችን ካላሻገርን፤ አርሶ አደሩ ከተለመደው ግብርና ሊወጣ አይችልም"

- አቶ ዮሴፍ በላይነህ
የሲዳማ ክልል መስኖ ልማት ኤጀንሲ ስራ አስኪያጅ

ኃይሉ ሣህለድንግል



የሲዳማ ክልል በቡና፣ ቱሪዝም እና ኢንዱስትሪው ዘርፎች በእጅጉ ይታወቃል። ከክልሉ ከፍተኛ መጠን ያለው ቡና ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ ይቀርባል። የሀዋሳ ሀይቅ፣ የክልሉ ሕዝብ ባህላዊና ሌሎች የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የቱሪስት መስህቦች ደግሞ በቱሪዝም ዘርፍ የሚጠቀስ አርገውታል፤ ክልል ግዙፉን የሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ትላልቅ የኢንዱስትሪ ተቋማት ባለቤትም ነው።

ክልሉ ያሉትን እምቅ አቅሞች በማልማት ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን በመስኖ ልማት ላይ በትኩረት እየሰራ ይገኛል። ያሉትን ትላልቅ ወንዞች፣ የከርሰ ምድር ውሃ ሀብትና የሀዋሳን ሀይቅን ለመስኖ ልማት ለማዋል መስራቱን ተያይዞታል። ለእዚህም ሰፋፊ የአለኝታና የዝርዝር ጥናት ስራዎችን እያካሄደ ከመሆኑ በተጨማሪ ወደ መስኖ ልማቱም ተሸጋግሯል።

በሲዳማ ክልል ከመስኖ መሰረተ ልማት አኳያ የተለያዩ ተግባሮች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በግድብና ለመስኖ በሚውል አካባቢ ጥናት፣ በጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ የሀዋሳ ሀይቅን ለበጋ ስንዴ ልማት በማዋልና በመሳሰሉት ላይ እየተከናወኑ ባሉ ተግባሮች ዙሪያ ከክልሉ መስኖ ልማት ኤጀንሲ ስራ አስኪያጅ አቶ ዮሴፍ በላይነህ ጋር ያደረግነውን ቆይታ በወቅታዊ አምዳችን ለንባብ አብቅተነዋል።

**የሀዋሳ ሀይቅን አርሶ አደሩ ለረጅም ጊዜ ትናንሽ ፓምፖችን በመጠቀም ለመስኖ ሲያውለው ቆይቷል፤ ይህ ማለት ጨዋማነት አላቆመውም ይህ አንዱ የጥናት አካል ነው**

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ በክልሉ ለመስኖ ልማት እየተከናወኑ ባሉ ስራዎች ዙሪያ በተለይ የመስኖ ልማት ሊካሄድባቸው በታሰቡ አካባቢዎችና ለእዚህም በሚያስፈልጉ የመስኖ መሰረተ ልማቶች ዙሪያ በጥናትና ልዩታ በኩል እየተከናወነ ስለሚገኙ ተግባሮች ጠቅለል ያለ ማብራሪያ ቢሰጡን።**

**አቶ ዮሴፍ፡-** ከመስኖ አኳያ በክልሉ አንደኛ ደረጃ አድርገን የምንሰራው በመስኖ ሊለማ የሚችል ምን ያህል አቅም እንዳለ መለየት ነው። በገጸ ምድር እና በከርሰ ምድር ውሃ መልማት የሚችለውን መሬት በመለየት ይሰራል። የትኛው ውሃ ምን ያህል መሬት ያለማል በሚለው ላይ የአለኝታና ዝርዝር ጥናት እንሰራለን።

ወደ ዝርዝር ጥናት ሳይገባ ያለውን አቅም ለማወቅ የሚሰራ ቅድመ ጥናት የሚባል ነገር አለ። በክልሉ ዝናብ አጠር ወረዳዎች አሉ። በእነዚህ አካባቢዎች ምን ያህል በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት አለ፤ ለእዚህ የሚሆን ምን የውሃ አቅም አለ በሚለው ላይም በሰባት ወረዳዎች የጥናት ስራዎችን ጀምረናል። በእነዚህም ከጥቁር ውሃ እስከ ዳራ ወረዳ ባሉት የታችኛው የክልሉ ወረዳዎች ለመስኖ ሊውል የሚችል ምን ያህል መሬት አለ የሚለው ጥናት ተጀምሯል።

**አዲስ ዘመን፡- እስከ አሁን በወረዳዎቹ የተካሄዱት ጥናቶች ምን አመላከቱ። በቀጣይስ ምን ለመስራት ታስቧል?**

**አቶ ዮሴፍ፡-** በዚህም ጥናት በወረዳዎቹ በከርሰ ምድርና በገጸ ምድር ውሃ በመስኖ ሊለማ የሚችል 27 ሺ ሄክታር መሬት መኖሩ ታውቋል። ይህ ልይታ ከተደረገ በኋላም ወደ ዝርዝር ጥናት ተገብቷል።

ዝርዝር ጥናት ከሚካሄድባቸው መካከል በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ የሚካሄደው የከርሰ ምድር ውሃ አንዱ ነው፤ ሌላው ደግሞ መካከለኛ መስኖ ነው፤ ይህም በጂጌሳ ወንዝ ላይ የሚገነባ ነው። ዋንሞሌ ወንዝ ላይ የሚገነባም አለ። የጠቀስኳቸው ፕሮጀክቶች ትላልቅ ናቸው። ጊዳቦ እና ኮላ ወንዝ ላይ የሚገነቡ የመስኖ ፕሮጀክቶችም አሉን። አነስተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶችን እየገነባን የሕዝቡን ፍላጎት ማሟላት አንችልም፤ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን መገንባት አለብን ብለን እነዚህን ትላልቅ ፕሮጀክቶች ለመገንባት እየሰራን እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን፡- ዝርዝር ጥናት እየተካሄደባቸው ያሉ ፕሮጀክቶች የትኞቹ ናቸው?**

**አቶ ዮሴፍ፡-** ወደ አስራ ስምንት የሚሆኑ የመካከለኛና አነስተኛ ፕሮጀክቶች ዝርዝር ጥናቶች በተለያዩ ወረዳዎች እየተካሄዱ ናቸው። ጥናታቸው ሲጠናቀቅ እንደሚገኘው የመንግስት በጀት ወደ ግንባታ ይገባል፤ ለተለያዩ ድጋፎች ለሚመጡ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሚሆኑ ጥናቶችን አድርገን ሰነዶቹን መደርደሪያ ላይ እናስቀምጣለን። ይህም ገንዘብ ይዘው ለሚመጡ አካላት ጥናት የለንም የሚል ምላሽ ከመስጠት ያወጣናል። የሚመጣ ሀብትን ፈጥነን ለመጠቀም ያስችለናል።

በተጨማሪም ክልሉ ከተለያዩ ረጂ ተቋማት ያገኛቸው ወደ 40 የሚሆኑ የውሃ መሳቢያ ሞተሮች አሉት። እነዚህ የውሃ ፓንፓች ከ30 ሄክታር የማያንስ ማልማት ያስችላሉ። በክልሉ አንድ አርሶ አደር 30 ሄክታር የለውም፤ ሁለት አርሶ አደሮችም ሆነው 30 ሄክታር መሬት አይኖራቸውም። እነዚህን ፓምፖች አርሶ አደሮችን አደራጅተንና አስተሳስረን 30 የሚሆኑ አርሶ አደሮች መሬት ተደምሮ 30 ሄክታር እንደሚሆን ታስቦ ለእነሱ ለመስጠት ስርዓት ለማበጀት እየተሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በመስኖ ልማት ኤጀንሲው በኩል ምን ያህል ፕሮጀክቶች እየተካሄዱ ናቸው?**

**አቶ ዮሴፍ፡-** በሲዳማ ክልል መስኖ ልማት ኤጀንሲ ስር ወደ 26 የግንባታ ፕሮጀክቶች አሉ። እነዚህ ፕሮጀክቶች ተገንብተው ሲጠናቀቁ ከአራት ሺ 355 ሄክታር በላይ መሬት ማልማት ያስችላሉ። ፕሮጀክቶቹ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ቢሆኑም እስከሚጠናቀቁ መጠበቅ ውስጥ አልተገባም፤ አንዳንዶቹ በከፊል አገልግሎት እንዲሰጡ እየተደረገ ግንባታቸው ቀጥሏል።

**አዲስ ዘመን፡- የፕሮጀክቶቹ የግንባታ አፈጻጸም በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**አቶ ዮሴፍ፡-** እነዚህ ፕሮጀክቶች በሁለት መሰረታዊ ችግሮች በተባለው የጊዜ ሰሌዳ በውሉ መሰረት እየተፈጸሙ አይደሉም፤ የኮንትራክተሮች የመፈጸም አቅም ዝቅተኛነት አንዱ ተግዳሮት ነው። ሁለተኛው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች ቢኖሩም ከሲሚንቶ ጋር በተገናኘ የሚታየው የአቅርቦት ችግር ነው።

እንደሚታወቀው የመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታ ከፍተኛ መጠን ያለው ሲሚንቶ ይፈልጋል። በሀገር ውስጥ የተፈጠረው የሲሚንቶ እጥረትና ውል ሲገባ የተያዘው ገንዘብ መጠን በመቶና ሁለት መቶ በመቶ መጨመሩ ከእኛ ጋር ውል ገብተው በሚሰሩት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል። በዚህም የተነሳ ተቋራጮቹ በአግባቡ መስራት አልቻሉም።

በውላችን መሰረት ስራዎች እንዲከናወኑ ተገቢውን ክትትልና እርምጃ እየወሰድን ቢሆንም፣ እነዚህን ነገሮች ለመፈጸም የአቅም ውስንነት አጋጥሟል። ከእዚህም የተነሳ አንዳንድ ተቋራጮች ከውሉ ውጭ ዋጋ እንዲስተካከል ጥያቄ እያቀረቡ ናቸው፤ እነዚህ ችግሮች ፕሮጀክቶች እንዲጓተቱ አድርገዋል። ሲሚንቶና የአቅም ውስንነት ትልቅ ችግር ሆኖብናል። በአጠቃላይ ችግሩ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተገንብተው ለአርሶ አደሮችም ሆነ ለፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ክፍሎች እንዳይደርሱ እያደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የጊዳቦ ግድብ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መመረቁ ይታወቃል። ይሁንና በሲዳማ ክልል በኩል ያለው የግንባታው ስራ እንዳልተጠናቀቀና የሚፈለገውን ልማት ለማካሄድ እንዳልተቻለ እየተነገረ ይገኛል። ግንባታው አለመጠናቀቁ በግድቡ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃንን በዘመናዊ መስኖ ለማሰማራት በሚያስችለውና በቅርቡ ወደ ስራ በገባው ፕሮጀክት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያሳርፍ ስጋት አሳድሯል። ግንባታው ለምንድን ነው ያልተጠናቀቀው?**

**አቶ ዮሴፍ፡-** በፌዴራል መንግስት እየተገነባ ያለው የጊዳቦ ግድብ የክልሉ አንዱ የመስኖ መሰረተ ልማት ነው። ይህ ፕሮጀክት የሚገነባበት አካባቢ ስትራቴጂክ አካባቢ ነው። ሆኖም የጊዳቦ ግድብ ፕሮጀክት በሚፈለገው ጊዜ ተጠናቆ የሚፈለገውን አገልግሎት እየሰጠ አይደለም። አሁንም ድረስ በግንባታ ሂደት ላይ ከፍተኛ መጓተት ይታይበታል።

ግድቡ በሲዳማ ክልል በኩል አምስት ሺ ሄክታር ሊያለማ ይችላል። ይህ ቀላል አይደለም። ከአምስት ሺ ሄክታር መሬት ላይ ያለምንም ስጋት በዝናብ እጥረት እና በመሳሰለው ሳይባል ያለምንም የውሃ ችግር አምርተን ለገበያ ማቅረብ ስንችል በግድቡ ግንባታ አለመጠናቀቅ ሳቢያ ማልማትና ለገበያ ማቅረብ አልቻልንም። ይህ ልንታገለው የሚገባ ጉዳይ ነው። ፕሮጀክቱ የራሱ በጀት አለው። የሚያስፈልገው ክትትል ከተደረገለት ተጠናቆ

# ወቅታዊ

ለህብረተሰቡ መድረስ ይችላል።

ወጣቶችን አደራጅተን በዚያ አካባቢ በዘመናዊ የመስኖ ልማት ለማሰማራት እየተንቀሳቀስን ነው። በዚህች ሀገር ስራ አጥነት ምን ያህል አስቸጋሪና ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ስለመሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። ወጣቱን አደራጅተን እናሰማራበታለን ያልነው ፕሮጀክት እስከ አሁን ግንባታው ባለመጠናቀቁ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም።

ይህን ፕሮጀክት በባለቤትነት እያስገነባ ያለው የፌዴራል መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ነው። ግንባታውን እያካሄደ ያለውም የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ድርጅት ነው። ሁሉቱም የመንግስት ተቋማት ናቸው። አማካሪውም የመንግስት ተቋም ነው። ስለዚህ ይህንን ችግር ልዩ ትኩረት በመስጠት መፍታት እየተቻለ መሄድ ያለበትን ያህል እየሄደ አይደለም የሚል ግምገማ አለን። በዚህ ጉዳይ ላይ በተደጋጋሚ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር ተወያይተንበታል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁንስ መፍትሄው ምንድነው ይላሉ?**

**አቶ ዮሴፍ፡-** ይህን ፕሮጀክት በተመለከተ ያለው ተስፋ በቅርቡ ይፋ ተደርጓል፤ ስለዚህ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ ፕሮጀክት ስለመጣ ለእዚህ ፕሮጀክት ለምናደርገው ርብርብ ተጨማሪ አቅም አግኝተናል እላለሁ። ቀጥሎ የተሻለ ተስፋ ይኖራል የሚል እምነት አለኝ። ምክንያቱም ቀሪ ስራዎችን የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፍላጎቶች አሳይተዋል፤ ከአፍሪካ ልማት ባንክና ከተባበሩት አረብ ኤምሬት ባንክ ጋር ግንኙነት መፍጠር ከተቻለ ተስፋ ይኖራል።

ፕሮጀክቱ ይጠናቀቃል የሚል እምነት ቢኖረንም፣ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ መሬቱ ወደ ስራ ገብቶ ቢሆን ተጨማሪ አቅም ማግኘት እንችል ነበር፤ ያንን ሀብት አጥተናል። በቀጣይም በእዚህ አካባቢ ላይ በትኩረት ይሰራል፤ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ጋር እየተናበብን ያለንበት አግባብም አለ።

**አዲስ ዘመን፡- የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት በቆላማው የሀገሪቱ አካባቢ ተጀምሮ በደጋና ወይናደጋው አካባቢም በስፋት እየተካሄደ ይገኛል። በክልሉ ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የሚውሉ የመስኖ መሰረተ ልማቶችን ከመገንባትና ወደ ስራ ከማስገባት አኳያ ምን እየተከናወነ ነው?**

**አቶ ዮሴፍ፡-** በሲዳማ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ተጀምሯል። ልማቱ በሰፊው ከሚካሄድባቸው አካባቢዎች አንዱ የሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ነው። ይህን ለመስራት ከሀዋሳ ሀይቅ በሶስት መስመር ውሃውን በሞተር ፓምፕ በመውሰድ በሀይቁ ዙሪያ ያለውን መሬት እንዲያለማ አድርገናል።

ሁለተኛ በዚሁ አካባቢ አምስት መቶ ሜትር ጥልቀት ካለው ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ውሃ አውጥተናል። ጉድጓዱ በሰከንድ አንድ መቶ ሊትር ውሃ ማምረት ያስችላል። ይህ ውሃ ማለት ትልቅ ሀብት ነው፤ ለበጋ መስኖ ልማት ብቻ ሳይሆን ለየትኛውም ወቅት መጠቀም የሚያስችል ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ወጥቶበት የተሰራና ለረጅም ጊዜ አገልግሎት መስጠት የሚችልም ነው።

ሌላም አምስት መቶ ሜትር ጥልቀት ያለው ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ግንባታ በዚሁ የሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ እያስገነባን እንገኛለን። በወረዳው 240 ሜትር ጥልቀት ያለው ሌላ ጥልቅ የውሃ ጉድጓድም አስገንብተናል። አካባቢው ቆላማ ነው፤ እንደ ክልል በዚያ አካባቢ ዝናብ ጠብቀን ብቻ ለምን እናለምለን የሚል አቋም ተይዞ ነው ወደዚህ ስራ የተገባው። በዚህም በኮንስትራክሽን በኩል ውጤታማ ተግባር ተከናውኗል።

የተገኘው ውሃ ምን ያህል ያለማል ለሚለው እንደ የአጠቃቀማችን ነው የሚወሰነው። በሰከንድ 100 ሊትር ማለት ቀላል አይደለም። ያላለቁ ፕሮጀክቶችም አሉን። አንዱ ያለቀው ማልማት ጀምሯል፤ ሄዶ ማየት ይቻላል። ነገር ግን ዘንድሮ ለበጋ ስንዴ መስኖ ልማት እየተጠቀምን በዘላቂነት አርሶ አደሩ በማይጠቀምበት ሰዓት ገንዳ ተገንብቶ ውሃው የሚጠራቀምበት ከዚያም ሌላ ስትራክቸር ተገንብቶለት ውሃው ወደሚፈለገው ቦታ የሚሄድበት ስራ በቀጣይነት የሚከናወን ይሆናል።

የጥልቅ ጉድጓድ ውሃ ጥቅም ላይ እየዋለ ሲሄድ ይጎላል የሚባል ነገር አለ። እነዚህ ጉድጓዶች ግን እንደእዚህ አይነት ባህሪ የላቸውም። ውሃቸው አይጎልም፤ ስለዚህ ማልማት የምንችለውን ያህል

> **ሰፊው የሲዳማ ክፍል በቂ የዝናብ መጠን ያገኛል፤ ዝናቡ ግን ወጣ ገባነት አለበት። በእዚህ የተነሳም የአርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነት እየቀነሰ ነው። በዝናብ እጥረት የሚቸገሩ አካባቢዎችም አሉ። ይህን ችግር ለመፍታት ውሃ በመያዝ አርሶ አደሩ እንዲጠቀም ማድረግ ይቻላል ተብሎ እየተሰራ ይገኛል።**

ማመንጨት እንችላለን። ይህ ማለት ለጥልቅ ውሃው የምናስገባቸው የውሃ መሳቢያዎች በቀን ከ16 እስከ 18 ሰዓት የሚሰሩ ከሆነ በማታውም ፈረቃ ውሃውን ማውጣት እንችላለን። የተወሰነ ሰዓት እያሳረፍን ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ጉድጓዱ ብዙ መሬት ያለማል ብለን እንገምታለን።

ሎካ አባያ ወረዳ አካባቢም እንዲሁ ተመሳሳይ ስራ እየተሰራ ነው። በአጠቃላይ እነዚህን በተመለከተ ለበጋ መስኖ ለዘንድሮ ብቻ ተብሎ የሚሰራ አይደለም። እነዚህ ስራዎች ዘንድሮ በተገነቡበት አካባቢ በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሌላ መሰረተ ልማት እንዳይጠይቁ አርገን ነው የሰራናቸው። በዚህ አቅድ መሰረት በእነዚህ አካባቢዎች ስንዴ ተዘርቷል።

**አዲስ ዘመን፡- ውሃውን ስመስኖ አገልግሎት በመጠቀም በኩል ከመስኖ ቴክኖሎጂ አንጻርስ ምን እየሰራችሁ ነው?**

**አቶ ዮሴፍ፡-** ቅድም ያነሳሁልህ እየተገነቡ ያሉ 26 የመስኖ መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ለሚፈለገው ቦታ ውሃ የሚያደርሱት ደረጃቸውን የጠበቁ ካናሎች ተገንብተውላቸው ነው። ሀዋሳ ዙሪያ ላይ ከድሪፕ ወይም ስፕሪንት የቱ ይሻላል በሚለው ላይ ጥናት እየተደረገ ነው። የሀዋሳ ዙሪያ አፈር በካናል የሚችል አይነት ስላልሆነ ነው ጥናት ማድረግ ያስፈለገው። ሌሎች የመስኖ መሰረተ ልማቶች ግን ደረጃውን የጠበቀ ግንባታ ተደርጎላቸዋል። የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችም በአካባቢዎቹ ይካሄዳሉ።

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ መስኖ በስፋት ይካሄድባቸዋል ተብለው የተለዩ አካባቢዎች የትኞቹ ናቸው? ስአካባቢዎቹ የታሰቡት የመስኖ መሰረተ ልማቶቹ ምንድን ናቸው?**

**አቶ ዮሴፍ፡-** በቀጣይ በስፋት ይሰራሉ ተብለው በመስኖ ልማት በኩል ከሚታሰብባቸው አካባቢዎች አንዱ የሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ነው። በወረዳው የከርሰ ምድር ውሃ ፕሮጀክቶችን በስፋት ወደ ስራ እናስገባለን። አለታ ጩኮና ዳራ ቶልቻ የሚባለው ወረዳ ውስጥ ያለውን ጂጌሳ የሚባል ወንዝ ለመስኖ ለመጠቀም በፌዴራል ተቋም ጥናት እያሰራን ነው። ይህ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ ሰፊ መሬት ያለማል ብለን ተስፋ አድርገናል። ወደ ግንባታ ለማስገባት ትኩረት አድርገን እንሰራለን። ዳሌ እና ሸበዲኖ ወረዳዎች ላይም እንዲሁ ትላልቅ ፕሮጀክቶች አሉን።

**አዲስ ዘመን፡- በመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታ ያጋጥማል ብላችሁ ያሰባችሁት ተግዳሮት አለ? ተግዳሮቱ ካለ እንዴት ልትፈቱት አሰባችኋል?**

**አቶ ዮሴፍ፡-** እነዚህ ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ ሲገቡ እንደ ሲዳማ ክልል ተግዳሮቶች ይገጥሙናል ብለን አስበናል። እንደሚታወቀው በሲዳማ ክልል ሕዝብ ያልሰፈረበት መሬት የለም። መሬቱ አርሶ አደሩ ቡና፣ እንሰትና የመሳሰሉትን ተክሎ በንብረት ይዞታል። ወደ ግንባታ በሚገባበት ጊዜ ይህን ሁሉ አርሶ አደር አስነስቶ ግንባታውን ማካሄድ ፈተና ሊሆን ይችላል። ለአብነትም አንድ "ቢሳንዲማ" የሚባል ፕሮጀክት አለን። ይህ ግድብ ለሚሰራበት ቦታ ብቻ 72 ሄክታር መሬት ያስፈልገዋል። በዚህ 72 ሄክታር መሬት ላይ ቡና፣ እንሰት፣ ጫትና የመሳሰሉት ቋሚ ተክሎች አሉበት፤ አርሶ አደሩም ቤት ሰርቶ ይኖራል። ለእዚህ አርሶ አደር ካሳ ከፍለህ፣ አንስተህ ሌላ ቦታ አስፍረህ ካናሉን ተከትሎ ካለው አካባቢ አርሶ አደሩን ማንሳት ትልቅ ፈተና ነው። ይሄ ፈተና በሌሎች አካባቢዎች እንደሚስተዋለው አይነት አይደለም፤ ሲዳማ ውስጥ የመሬት ጥበት አለ። ይሄ ትልቁ ፈተናችን ይሆናል ብለን እናስባለን።

ፈተናው ቢኖርም ፈተናውን ተጋፍጠን፣ የሚገነባውን ገንብተን አርሶ አደሮቻችን ካላሻገርን በመደበኛው መንገድ የምንሄድ ከሆነ አርሶ አደሩ ከተለመደው የግብርና ስራ ሊወጣ አይችልም፤ ይህ ደግሞ ለውጥ ማምጣት አያስችልም። ስለዚህ እንደዚህ አይነት ስራዎች ሲሰሩ ጠንከር ያሉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፤ ለዚህም አርሶ አደሩ እንዳይፈናቀል የሚያስችል ተገቢውን የካሳ ስርዓት ዘርግተን እንሰራለን። የዚህ መሰኖ ፕሮጀክት ጥናት ከ75 በመቶ በላይ ተጠናቅቋል። ፕሮጀክቱ በፌዴራል መንግስትና በክልሉ በበጀት የሚደገፍና ከፍተኛ ካፒታል የሚፈልግ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የመሰረተ ልማት ግንባታ በባህሪው ከፍተኛ መጠን ያለው ፋይናንስ ይፈልጋልና ከዚህ አኳያ በፋይናንስ በኩል ምን ታቅዷል?**

**አቶ ዮሴፍ፡-** ሁለት እጥረቶች ይከሰታሉ ብለን እናስባለን። አንደኛው ሰፊ ነጻ መሬት አለመኖሩ ነው። ሁለተኛው የካፒታል እጥረት ነው። የጊዳቦ ግድብ ቀሪ ስራዎችን ለመጨረስ ብቻ ከ900ሚሊየን ብር በላይ ያስፈልጋል፤ ሰከንዳሪና ተሪሸሪ ካናሎችን ለመገንባት።

የመስኖ ስራ የግድብ ግንባታ ሊያስፈልገው ይችላል፤ የካናል ግንባታ አለው። በባህሪው ቢሊየን ብሮችን ይፈልጋል። ስራ ላይ የሚውሉት ግብአቶች አብዛኞቹ የፋብሪካ ውጤቶች ናቸው። ይሄ ከፍተኛ የመነሻ ካፒታል ይፈልጋል። ግንባታዎቹ ጥሩነቱ ከተጠናቀቁ በኋላ ብልሽት ሊያጋጥማቸው የሚችልበት ሁኔታ ዝቅተኛ ነው። ስታንዳርዱ ተጠብቆ በቂ ክትትል ተደርጎለት ከተሰራ ለረጅም ጊዜ ሳይበላሽ ይቆያል። አንዴ ከተሰራ ለረጅም ጊዜ መጠቀም ያስችላል።

ከፋይናንስ ምንጭ ጋር በተገናኘ ሁለት እድሎች ይኖራሉ። አንደኛ እንደ ሀገር ለዘርፉ የተሰጠውን ትኩረት ይዘን እቅድ ስናቀርብ ይታያል፤ ዘመኑ ደግሞ እንደ ክልልም ለመስኖ ትኩረት ሰጥቷል። ሁለተኛ ከፌዴራል መንግስት ጋር ከፌዴራል "ኤስዴጂ" ከተባለ ፕሮግራም ጋርም ይሰራል፤ ቅድም የጠቀስኳቸው ከሁለትና ሶስት ፕሮጀክቶች ውጪ ያሉት 26 ፕሮጀክቶች በእዚህ መልኩ የሚሰሩ ናቸው።

ኤሲዲጂ በሚባል ፕሮግራም ከገንዘብ ሚኒስቴር ለሁሉም ክልሎች የሚሰጥ በጀት አለ። በዚህ በጀት ነው ስራዎቹ እየተሰሩ ያሉት። እነዚህን ፕሮጀክቶች ለአነስተኛ ፕሮጀክቶች ብቻ ከምናውል ብለን መካከለኛ ለሚባሉ ፕሮጀክቶችም አስገብተን የክልሉን አቅም አክለን ለመስራት አቅደን እየሰራን ነው።

እነዚህ ፕሮጀክቶች የሚታዩት ጥናታቸው ተጠናቆ ለሚመለከታቸው አካላት ሲቀርቡ ነው። ያኔ የፕሮጀክቶቹ አዋጭነት ሲታመንበት የገንዘብ ምንጩም ይታያል። ሁለተኛ ጥናት ሲያልቅ ለፌዴራል ቆላማ አካባቢና መስኖ ሚኒስቴር እናቀርባለን። እነሱ በክልሎች ፕሮጀክቶችን ስለሚገነቡ ለእዚህም ድጋፍ እንዲደረግልን እንጠይቃለን።

**አዲስ ዘመን፡- በጊዳቦ ግድብ በአሁኑ ወቅት ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ዮሴፍ ፡-** የጊዳቦ ግድብ እስከሚጠናቀቅ እኛ የምናስተዳድረው ዲዛይኑን እና ስትራክቸሩን ነው። ባለሀብቶች እየሰሩ ያሉበት ሁኔታ አለ። የክልሉ መንግስት በአካባቢው እየሰሩ ካሉት ባለሀብቶች ማነው ውጤታማ በሆነ መልኩ እየሰራ ያለው የሚል ጥናት እያካሄደ ነው።

አካባቢው ቀደም ሲል የኢንቨስትመንት ኮርደር በሚል የተያዘ ነበር። ኢንቨስተሮች በአካባቢው የተሰማሩት በደቡብ ክልል ስር በነበረበት ወቅት ነው። ፕሮጀክቱ እያለቀ ሲመጣ ወጣቶች በዚህ ዘርፍ ተጠቃሚ ይሁኑ ሲባል መንግስት ትኩረት አድርጎ ይህን ችግር በመፍታት ለወጣቶች ለማስተላለፍ አቋም ይዟል። ስለዚህ በዚህ በኩል ብዙ ችግር ይገጥመናል ብለን አናስብም።

**አዲስ ዘመን፡- ሲዳማ ክልል ጥሩ ዝናብ አለው፤ ትላልቅ ወንዞችም አሉት ይባላል፤ እነዚህን እምቅ አቅሞች እንዴት ልትሰሩባቸው አስባችኋል፤ ጊዳቦ ላይ ሌላ ግድብ የመስራት ሀሳብ አለ።**

**አቶ ዮሴፍ፡-** ሰፊው የሲዳማ ክፍል በቂ የዝናብ መጠን ያገኛል፤ ዝናቡ ግን ወጣ ገባነት አለበት። በእዚህ የተነሳም የአርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነት እየቀነሰ ነው። በዝናብ እጥረት የሚቸገሩ አካባቢዎችም አሉ። ይህን ችግር ለመፍታት ውሃ በመያዝ አርሶ አደሩ እንዲጠቀም ማድረግ ይቻላል ተብሎ እየተሰራ ይገኛል።

ሲዳማ ውስጥ ያሉት ወንዞች አብዛኞቹ ሸለቆ ውስጥ ናቸው። በቀላሉ አውጥተን የምንጠቀማቸው አይደሉም። ከወጡም በኋላ የሚያለሙት ሜዳማ መሬት አያገኙም። እንደዚህ አይነት ቦታዎች ላይ ውሃ ስትለቅ አካባቢውን አጥቦ ይሄዳል። ስለዚህ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል። በመስኖ ስራ ውስጥ የመሬት አቀማመጥ ከፍተኛ ተጽእኖ አለው።

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ የመስኖ ልማት ማካሄድ ምን ያህል አዋጭ ነው ብለው ያምናሉ።**

**አቶ ዮሴፍ፡-** እንደሚታወቀው አዋጭ ነው፤ ምን ያህል ተጨማሪ አቅም ይሆናል ለሚለው አንድ አርሶ አደር አንድ ሄክታር ቢኖረው በአመት አንዴ የሚያርስ ከሆነ የሚያለማው አንድ ሄክታር ነው። ተጨማሪ ውሃ አግኝቶ በሚፈለገው ውሃ ማረስ ቢችል በአመት በአንድ ሄክታር ላይ የሁለት ሄክታር ምርት ያመርታል። ሶስቴም ሊያመርት ይችላል። ሶስት ሄክታር ይሆንለታል። ስለዚህ የመስኖ ልማት ለእንደዚህ አይነት ማህበረሰብ ከፍተኛ ፋይዳ አለው ተብሎ ይወሰዳል። የመስኖ ልማት ለትናንሽ ማሳዎች ትልቅ ፋይዳ አለው። አርሶ አደሮቹ መሬታቸውን በተደጋጋሚ መጠቀም ያስችላቸዋል።

**አዲስ ዘመን ፡- የሀይቅ ውሃንና የጥልቅ ውሃ ጉድጓድን ስመስኖ ማዋል ከጨዋማነት ጋር ተያይዞ ችግር ሲከሰት ይችላል የሚሉ ወገኖች አሉ። ክልሉ የሀዋሳ ሀይቅንና ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችን ለመስኖ ልማት እያዋለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህ ችግር እንዳያጋጥም ምን እየተከናወነ ይገኛል? በሀይቁ ውሃስ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ዮሴፍ፡-** ከሀዋሳ ሀይቅ ጋር በተገናኘ እየተከናወነ ያለው የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ ስራ ገና አልተጠናቀቀም። ይህን የሚሰራው ተቋም በመጀመሪያ ከሀይቁ ጋር የውሃ ባላንስ ስራ ይሰራል። ምን ያህል ውሃ ወደ ሀይቁ ይገባል? በፓምፕ ከሀይቅ ወስደን ለማልማት ምን ያህል ውሃ እንወስዳለን? የሚለው ይታያል። የውሃ ባላንስ ሲባል አንዳንዴ የሀይቁ ውሃ በጣም ይሞላል፤ አንዳንዴ ደግሞ ይሸሻል። ሀይቁ ምን ያህል ውሃ ይይዛል፤ ምን ያህል ውሃ ይወጣል የሚለው ይጠናል። በዚህ ላይ በመመስረት የሚሰራ ይሆናል።

ሁለተኛው ከጨዋማነት/ ሳሊኒቲ/ ጋር የሚታዩ ነገሮች አሉ። በተለይ ከጨዋማነት /ሳሊኒቲ/ ጋር በተያያዘ ሀዋሳ ሀይቅ አካባቢ ጥናት እየተካሄደ ነው። ጥናቱ ተሰርቶ በቀጥታ ወደ ቁፋሮም አይገባም፤ የውሃው ኬሚካል ባህሪም ተጠንቶ ይቀርባል። የከርሰ ምድር ውሃ ጥናት ውሃ መኖር አለመኖሩን እንጂ የሚያሳይህ ውሃው ምን አይነት ኬሚካል እንዳለው አያሳይም፤ ውሃው ተቆፍሮ ከወጣ በኋላ ናሙና ተወስዶ ይመረመራል፤ እንዲህ አይነቱን ችግር በሂደት እናየዋለን።

በሌላ በኩል ደግሞ የሀዋሳ ሀይቅን አርሶ አደሩ ለረጅም ጊዜ ትናንሽ ፓምፖችን በመጠቀም ለመስኖ ሲያውለው ቆይቷል፤ ይህ ማለት ጨዋማነት አላቆመውም። ይህ አንድ የጥናት አካል ነው፤ ሁለተኛ የሼህ መሀመድ አላሙዲ የመስኖ ልማት ጥቁር ውሃ አካባቢ ከሀይቅ ማዶ አለ። ልማቱ በከርሰ ምድር ውሃ ነው የሚካሄደው፤ ከዚህም ናሙና ተውስዷል። በሀዋሳ ዙሪያ ከተቆፈሩ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችም ናሙና ተወስዷል፤ ከእነዚህም የሚያሰጋ ነገር አላገኘንም። ጥናቱ ሲጠናቀቅ ደግሞ እናየዋለን።

**አዲስ ዘመን፡- ስቃስ መጠይቁ ትብብር ስላደረጉልን እናመሰግናለን።**

**አቶ ዮሴፍ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ

## ሩሲያ የኑክሌር ጦር መሣሪያዎቿን ቤላሩስ ውስጥ ልታጠምድ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሩሲያ ስልታዊ የኑክሌር ጦር መሣሪያዎቿን በአጋሯ እና በጎረቤቷ ቤላሩስ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ እንዲተኮሱ ለማድረግ እንደምታጠምድ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን አስታወቁ።

እንደ ቢቢሲ ዘገባ ፕሬዚዳንት ፑቲን አሜሪካ የኑክሌር ጦር መሣሪያዎቿን በአውሮፓ አገራት ውስጥ ማስማራቷን በመጥቀስ፣ ይህ የሩሲያ ውሳኔ የኑክሌር ጦር መሣሪያን ለሌላ አገር ላለማስተላለፍ የተደረሰውን ስምምነት የሚጥስ አይደለም ማለታቸውን የሩሲያ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃንን በመጥቀስ ዘግቧል።

ፕሬዚዳንቱ ጨምረውም ሩሲያ ስልታዊዎቹን የኑክሌር ጦር መሣሪያዎቿን ቤላሩስ ውስጥ ታስማራ እንጂ፣ በእራሷ ቁጥጥር ስር እንደሚሆኑ ተናግረዋል።

ይህ የሩሲያ ውሳኔ ይፋ ከሆነ በኋላ፣ አሜሪካ ሩሲያ የኑክሌር ጦር መሣሪያዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል እየተዘጋጀች ነው ብላ እንደማታምን ገልጻለች።

የአሜሪካ የመከላከያ መሥሪያ ቤት ባወጣው መግለጫ ላይ «ያሉንን ስልታዊ የኑክሌር ጦር መሣሪያዎችን አቀማመጥ ለማስተካከል የሚያስገድደን ምንም ምክንያት አይታየንም» ብሏል።

ጨምሮም «ለኔቶ የጋራ የመከላከያ ስምምነት ያለን ተገዢነት ባለበት ይቀጥላል» በማለት ማንኛውም ውሳኔ ከሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን አገሮች ጋር የሚወሰን መሆኑንም አመልክቷል።

የጦር መሣሪያዎቹ የሚጠመዱባት የቤላሩስ መንግሥት ጠንካራ የሩሲያ ወዳጅ ሲሆን፣ በዩክሬን ላይ የፈጸመችውንም ወረራ ይደግፈዋል።

ፕሬዚዳንት ፑቲን ቅዳሜ ዕለት በቴሌቪዥን በተላለፈ ንግግራቸው የቤላሩሱ ፕሬዚዳንት አሌክሳንደር ሉካሼንኮ ሩሲያ አገራቸው ውስጥ ስልታዊ ኑክሌር መሣሪያዎችን እንድታስማራ ሲጠይቁ እንደነበር ገልጸዋል።

ይህ የሩሲያ ውሳኔ የተለየ እንዳልሆነ የጠቀሱት ፑቲን «አሜሪካኖች ተመሳሳይ ነገር ለአስርት ዓመታት ሲያደርጉ ቆይተዋል። ስልታዊ የኑክሌር ጦር መሣሪያዎቻቸውን ከረጅም ጊዜ በፊት ነው በወዳጆቻቸው አገራት ግዛት ውስጥ ያሰማሩት» ብለዋል።

ለእነዚህ የኑክሌር ጦር መሣሪያዎች ማከማቻ የሚውሉ ቦታዎችን በመጪው ሐምሌ መጀመሪያ ላይ ሩሲያ ገንብታ እንደምታጠናቅቅም ፑቲን ተናግረዋል።

ከወዲሁም የተወሰነ ቁጥር ያላቸው የኑክሌር ጦር መሣሪያዎችን ማስወንጨፍ የሚችሉ ኢስካንደር የተባሉ ሚሳኤሎች ወደ ቤላሩስ መወሰዳቸውን ገልጸዋል።

በዚህ የሩሲያ እርምጃ ከ30 ዓመታት ወዲህ ሩሲያ ከግዛቷ ውጪ የኑክሌር የጦር መሣሪያ ማስወንጨፊያ ማዕከል ሲኖራት የመጀመሪያው ይሆናል ተብሏል።

ከሦስት አስርት ዓመታት በፊት ሶቪየት ኅብረት ስትፈርስ የነበሯት የኑክሌር ጦር መሣሪያዎች ነፃ አገራት በሆኑት በሩሲያ፣ በዩክሬን፣ በቤላሩስ እና በካዛክስታን ውስጥ ነበሩ። ነገር ግን ሁሉም የኑክሌር አረሮች ወደ ሩሲያ እንዲመለሱ ተደርጓል።

ይህ የፑቲን ውሳኔ ይፋ የሆነው የዩክሬን ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዜሌንስኪ ከሩሲያ ጋር ለሚያካሂዱት ጦርነት ምዕራባውያን አጋሮቻቸው ተጨማሪ ወታደራዊ ድጋፍ እንዲሰጧቸው መጠየቃቸውን ተከትሎ ነው።

ከቀናት በፊት 18 የሚሆኑ አገራት በጦርነት ውስጥ ለምትገኘው ዩክሬን በአንድ ዓመት ውስጥ ቢያንስ አንድ ሚሊዮን የመድፍ ተተኳሽ ለመስጠት ስምምነት ፈርመዋል።

የመሣሪያ እና የተተኳሾች እጥረት የገጠማት የዩክሬን ፕሬዚዳንት ዜሌንስኪ ከአንድ የጃፓን ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፣ ሠራዊታቸው ተጨማሪ ተተኳሾችን እስኪያገኝ ድረስ በምሥራቅ በኩል ጉልህ ጥቃት ለመክፈት አይችልም ሲሉ ተናግረዋል።



## በሁለት የአሜሪካ ግዛቶች በተከሰተ ከባድ አውሎ ነፋስ 26 ሰዎች ሞቱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ደቡባዊ የአሜሪካ ግዛቶችን በመታው ከባድ አውሎ ነፋስ ምክንያት በሚሲሲፒ እና በአላባማ ውስጥ ቢያንስ የ26 ሰዎች ሕይወት ጠፋ።

በአሁኑ ወቅትም በአደጋው ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ፈልጎ የማዳን ጥረት እየተደረገ ሲሆን፣ የሚሲሲፒ ግዛትም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተደንግጎባታል።

በሚሲሲፒ ግዛት ውስጥ የምትገኘው ሮሊንግ ፎርክ የተባለችው ከተማ ከሞላ ጎደል የወደመች ሲሆን፣ ጎዳናዎች በከባድ አውሎ ነፋሱ ምክንያት ከጥቅም ውጪ በሆኑ መኪኖች፣ በቤቶች ፍርስራሾች እና በመስታወት ስብርባሪዎች ተሸፍነዋል።

ከባድ አውሎ ነፋሱ ግዛቶቹን የመታው ነዋሪዎች እንቅልፍ ላይ በነበሩበት እኩለ ሌሊት ላይ ስለነበረ የማስጠንቀቂያ ደወልን የሰማ አልነበረም ተብሏል።

ከአደጋው መትረፋቸውን ተአምር ነው ያሉት ፍራንሲስኮ ማክናይት የተባሉት ነዋሪም፣ በውድቅት ሌሊት የነቁት በከባዱ የአውሎ ነፋስ ድምጽ መሆኑን ገልጸው፣ የዚያን ዓይነት የነፋስ ድምጽ በሕይወታቸው ሰምተው እንደማያውቁ ተናግረዋል።

ነፋሱ ከአምስት እስከ አስር ደቂቃ ብቻ መቆየቱን የሚናገሩት ግለሰቡ በመታጠቢያ ቤታቸው ውስጥ ባለ ገንዳ ውስጥ ተደብቀው ነበር የተረፉት። በአሁኑ ወቅት ቤታቸው ሙሉ ለሙሉ ፈርሶ የመታጠቢያ ቤታቸው ሁለት ግድግዳዎች ብቻ ባሉበት ቆመው ይገኛሉ።

የሚሲሲፒ አገረ ገዢ ቴት ሪቭስ በከባዱ አውሎ ነፋስ የተመቱ የግዛቲቱን ከተሞች ቅዳሜ ዕለት በመጎብኘት ነዋሪዎችን ያነጋገሩ ሲሆን፣ የግዛቲቱ አስተዳዳሪ ያለውንም ሁኔታ «አሰቃቂ» ሲሉ በትዊተር ገጻቸው ላይ ገልጸውታል።

ተጨማሪ ከባድ አውሎ ነፋስ አላባማን እና ጆርጂያን እሁድ ዕለት ይመታል ተብሎ የተተነበየ ሲሆን፣ ቀደም ብሎ በመታቸው አካባቢዎች ከአደጋው የተረፉ ሰዎችን ፈልጎ የማዳን ጥረት እንደሚቀጥልም ተነግሯል።

አደጋውን ተከትሎ ከሚሲሲፒ የደረሳቸው መልዕክት «ልብ የሚሰብር ነው» ያሉት ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን፣ የፌዴራል መንግሥቱ ጉዳት የደረሰባቸውን ለመደገፍ «የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል» ሲሉ ቃል ገብተዋል።

**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር**
**በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**

# የግል ትምህርት ተቋማት የአሰራር ረቂቅ ደንብ

**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**

ትምህርት ለአንድ ሀገር የወደፊት የብልፅግና ጉዞ ትልቁን ሚና ይጫወታል፡፡ አሁን ባለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ቴክኖሎጂ እጅጉን ዘምኖ የሰው ልጅ የአኗኗር ዘይቤም በዚያው ልክ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ከሆነ ወል አደር ብሏል፡፡ በእውቀት ላይ የተመሰረተ የአመራር ብቃት ያላቸው የወደፊት ሀገር ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት ዛሬ በትምህርት ዘርፉ ላይ የሚሰራው ስራ ዋናውን ቦታ ይይዛል፡፡

በመዲናችን አዲስ አበባ ትምህርትን ተደራሽ ለማድረግ በርካታ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ በመንግስት ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ከመገንባት ጀምሮ ከዚህ ቀደም የተገነቡ ትምህርት ቤቶች የመቀበል አቅማቸውን ለማሳደግ ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች ሲገነቡ ቆይተዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ታዲያ ትምህርትን ለሁሉም ዜጋ እኩል ተደራሽ ከማድረግ አንፃር የመንግስት ጥረት ብቻውን በቂ ባለመሆኑ የግሉን ዘርፍም በትምህርት ዘርፉ በማሳተፍ ተደራሽነቱን ማስፋት አስፈላጊ ነው በመሆኑ ይህንን ተከትሎ በርካታ የግል ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ተቀብለው በተለያየ ደረጃ በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡፡ ታዲያ እነዚህ የግል ትምህርት ተቋማት ጥራት ያለውና ትምህርት ሚኒስቴር የሚያስቀምጣቸውን መመሪያዎች ተከትለው በዘርፉ እንዲሰሩ ራሱን የቻለ የአሰራር ደንብ ሊኖር ግድ ይላል፡፡

ይህንን ተከትሎ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን መጋቢት ዘጠኝ ቀን 2015 ዓ.ም የግል ትምህርት ተቋማት አሰራርን ለመምራት በተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ዙሪያ ውይይት አካሂዷል። በውይይቱ የግል ትምህርት ቤት ባለሀብቶችን ጨምሮ የመምህራን እና የተማሪ ወላጅ ማህበር ተወካዮች፣ በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አመራሮችና ባለሙያዎች፣ መምህራን እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ ሆነዋል።



በመርሀ ግብሩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የባለስልጣኑ ዋና ስራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሕይወት ጉግሳ፤ የከተማውን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ የግል ትምህርት ተቋማት አሰራር ደንብ ባለመኖሩ ይህንኑ መሰረት በማድረግ ረቂቅ ደንቡ መዘጋጀቱን አስታውቀዋል።

እንደ ስራ አስኪያጇ ገለፃ፤ ረቂቅ ደንቡ በግል በትምህርት ተቋማት ሊተገበሩ የሚገባቸውን ተግባራት መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቶ በሚመለከታቸው የፍትህ አካላት አስተያየት የተሰጠበት ነው፡፡ ረቂቅ ደንቡ በዋናነት አዲሱን ስርአተ ትምህርት እና ቀደም ብሎ በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የነበረውን ነባር መመሪያ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ እና በውይይቱ የተነሱ ሀሳቦችን በማካተት ረቂቅ ደንቡ ለከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ለውሳኔ ይቀርባል።

የባለስልጣኑ ምክትል ስራ አስኪያጅ ወይዘሮ ፍቅርተ አበራ በበኩላቸው፤ ደንቡ በዋናነት የግል ትምህርት ተቋማት በከተማው የትምህርት ተደራሽነት ላይ እያበረከቱ የሚገኘውን አስተዋጽኦ ታሳቢ በማድረግ መዘጋጀቱን ጠቅሰው፤ ተቋማቱ የእውቅና ፍቃድ የሚሰጣቸው ከወጣው የመመዘኛ መስፈርት ውስጥ ሰባ አምስት በመቶ እና ከዚያ በላይ ካገኙ መሆኑን በረቂቅ ደንቡ መቀመጡን አስገንዝበዋል።

ተቋማቱ በትምህርት ሚኒስቴርና በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀውን ስርአተ ትምህርት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው በረቂቅ ደንቡ መካተቱን የተናገሩት ወይዘሮ ፍቅርተ፤ ለቅድመ አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁለት አመት የሚቆይ የእውቅና ፍቃድ የሚሰጥ ሲሆን ለሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በሶስት አመት የሚታደስ የእውቅና ፍቃድ እንደሚሰጥ አብራርተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አሊ ከማል፤ መንግስት ለትምህርት ልማት ስራው ውጤታማነት በሚያከናውናቸው የተለያዩ ተግባራት የግል ትምህርት ተቋማት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ እንደሚገኙ ገልጸው፤ በረቂቅ ደንቡ የግል ትምህርት ተቋማት በትምህርት ሚኒስቴር እና ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀውን ስርአተ ትምህርት ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው በመቀመጡ ቢሮው አፈጻጸሙን በአግባቡ እንደሚከታተል አመልክተዋል።

ከዚህ ቀደም አንዳንድ የግል ትምህርት ተቋማት የትምህርት ሚኒስቴር ካስቀመጠውን ስርዓተ ትምህርት ውጭ የራሳቸውን የትምህርት አይነቶች በመጨመር ሲያስተምሩ ይስተዋል ነበር፡፡ አሁን በተቀመጠው የአሰራር ረቂቅ ደንብ ግን ይህ በሚቀርፍ መልኩ የሚሰራ ሲሆን ሁሉም የግል ትምህርት ተቋማት በትምህርት ሚኒስቴርና በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀውን ስርአተ ትምህርት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ አንዳንድ ደረጃቸውን ያልጠበቁ የትምህርት ተቋማት በትምህርት ዘርፉ ውስጥ ገብተው ዘርፉን በሚፈለገው ደረጃ ለማሳደግ እንቅፋት እንዳይሆኑ በየጊዜው የሚደረግ ክትትልና ቁጥጥር ወሳኝነት አለው፡፡ ለዚህም ለቅድመ አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁለት አመት የሚቆይ የእውቅና ፍቃድ የሚሰጥ ሲሆን ለሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በሶስት አመት የሚታደስ የእውቅና ፍቃድ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

# ስፖርት





# መዲና ኢንሳ የቅድሚያ ለሴቶች ሩጫን ክብረወሰን ሰበረች

**አስማማው ግዛው**

በ20ኛው ሳፋሪኮም ቅድሚያ ለሴቶች የ5ኪሎ ሜትር የሩጫ ውድድር የዓለም ታዳጊዎች ቻምፒዮኗ አትሌት መዲና ኢንሳ የውድድሩን ክብረወሰን በመስበር አሸነፈች። ውድድሩ ትናንት መነሻና መድረሻውን ቦሌ አትላስ በማድረግ የተካሄደ ሲሆን፣ በጠንካራ ፉክክር ታጅቦ ሊጠናቀቅ ችሏል።

የዘንድሮ ውድድር የተካሄደው ለ20ኛ ጊዜ ሲሆን ከ15ሺ በላይ ሴቶች ተሳትፈውበታል። ውድድሩ የተካሄደው ቦታዬ፣ መብቴ፣ ድምጼ በሚል መሪቃል ሲሆን፤ በውድድሩ ከተለያዩ ክለቦች፣ ማሰልጠኛ ማዕከላትና ከግል ተወዳዳሪዎች የተውጣጡ 130 አትሌቶች ተሳትፈዋል። በውድድሩ በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ መድረኮች ስኬታማ የሆኑ አትሌቶች ከፍተኛ ፉክክርን በማሳየት ውድድራቸውን ጨርሰዋል። ውድድሩ ታላቁ ሩጫ ከሚያዘጋጃቸው ውድድሮች በትልቅነቱ የሁለተኛነት ደረጃን እንደሚይዝም ተጠቁሟል።

በሳፋሪኮም ቅድሚያ ለሴቶች የ5 ኪሎ ሜትር ውድድር በተምሳሌት ሴቶች ዘርፍ ከ20 በላይ ስኬታማ ሴቶች ተሳትፈዋል። በውድድሩ 28 አካልጉዳተኛ ሴቶችና የ11 አገራት ሴት አምባሳደሮችም መሳተፍ ችለዋል። ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት 12 የጤና አፏፏጮችን በመመደብ የመሮጫ ሰዓቱን ለማፍጠን ሞክሯል።

በአዋቂ አትሌቶች መካከል በተደረገው ፉክክር በ2014 በታላቁ ሩጫ የ10 ኪሎ ሜትር ውድድርና በ2012 ቅድሚያ ለሴቶች ውድድር አሸናፊዋ ፅጌ ገብረሰላማ፣ የዓለም የታዳጊዎች ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ ባለቤት መልክናት ውዱ፣ እንዲሁም የታላቁ ሩጫን የ10ኪሎ ሜትር ሁለት ጊዜ ማሸነፍ የቻለችው ፎይቴን ተስፋይ ከፍተኛ ፉክክርን ማሳየት ችለዋል።



አትሌት መዲና ኢንሳ

ፎቶ፡- ሑዳሽ አብርሃ

በውድድሩ አትሌት መዲና ኢንሳ ከአማራ ማረሚያ የውድድሩን ክብረወሰን በመስበር አንደኛ ሆና ስታጠናቅቅ፣ ለአሸናፊነት ታጭታ የነበረችው አትሌት ፅጌ ገብረሰላማ ከአትዮ ኤሌክትሪክ ሁለተኛ ሆና ጨርሳለች። አትሌት መልክናት ውዱ ደግሞ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሦስተኛ በመሆን መጨረስ ችላለች።

አትሌት መዲና ሪከርዱን የሰበረችው 15:11:53 ሰዓት በመግባት ሲሆን የውድድሩ ክብረወሰን ባለቤት የነበረችውና የሁለት ጊዜ የውድድሩ አሸናፊ አትሌት ፋንታነሽ በላይ ነበረች። አትሌት ፋንታነሽ በላይ የቦታውን ክብረወሰን በ15:19:44 ይዛ የነበረ ቢሆንም አትሌት መዲና ኢንሳ በ7 ሰከንዶች በማሻሻል የግሏ ማድረግ ችላለች። አትሌት መዲና የዓለም ታዳጊዎች 5ሺ ሜትር ቻምፒዮን መሆኗ ይታወሳል።

የውድድሩ አሸናፊ አትሌት መዲና ኢንሳ የመጀመሪያ ተሳትፎዋ እንደሆነና ብዙ ዝግጅት እንዳላደረገች ገልጻለች። «ፉክክሩ በጣም ጥሩ ነበረ፤ ስላልተዘጋጀሁና ከእኔ የተሻሉ ልጆች ስለነበሩ አሸንፋለሁ ብዬ አለሰብኩም፤ ነገርግን መጨረሻ ላይ አቅም ስለነበረኝ አሸንፌያለሁ» ስትል አስተያየቷን ሰጥታለች። ውድድሩ ዕድል ላላገኙ አትሌቶች መታያ መሆኑንም ጨምራ ገልጻለች።

በውድድሩ ተጠብቃ የነበረችውና ከአንድ ወር በፊት በአውስትራሊያ ባትረስት በተከናወነው የ2023 የዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ አሸናፊ የሆነችው አትሌት ፅጌ ገብረሰላማ ከኢትዮ ኤሌክትሪክ ሁለተኛ በመሆን ጨርሳለች። ፅጌ ውድድሩን ከሦስት አመታት በፊት ያለምዘርፍ የኋላውን በጊዜው የቦታው ክብረወሰን በሆነ 15፡19.50 ሰዓት በመቅደም ካሸነፈች በኋላ የርቀቱን የትራክ ሰዓቷን ወደ 14፡43.90 ዝቅ አድርጋለች፡፡ በተጨማሪም ባለፈው ጥቅምት ወር ላይ በተከናወነው የቫሌንሺያ ግማሽ ማራቶን 01፡05፡46 በመግባት በሁለተኛነት ማጠናቀቋ ይታወሳል፡፡

በውድድሩ ሁለተኛ የወጣችውና የከዚህ ቀደሟ የውድድሩ አሸናፊ ፅጌ ገብረሰላማ ውድድሩ ቆንጆ እንደነበረና ለዚህ ውድድር ብላ አለመዘጋጀቷን ጠቁማለች። ለመጀመሪያ ጊዜ በተሳተፈችበት አንደኛ መውጣቷን ገልጻ፣ በአሁኑ ውድድር ትንሽ ህመም ስለተሰማት ተጽዕኖ እንዳሳደረባት ጠቁማለች።

በውድድሩ ሦስተኛ ደረጃን በመያዝ የጨረሰችው አትሌት መልክናት ውዱ በበኩሏ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ መሳተፏንና የመወዳደሪያ ቦታው ቁልቁለታማና ዳገታማ በመሆኑ ውድድሩ ከባድ እንደነበረ አስረድታለች። በውድድሩ መሳተፋችን ያለንበትን አቋም እንድንፈትሽና ለቀጣይ ውድድሮች ለመዘጋጀት ይጠቅመናል በማለት አስረድታለች። ለአሸናፊ አትሌቶች የ50ሺ ብር እና የዋንጫ ሽልማት ተበርክቷል። አንደኛ በመውጣት የውድድሩን ክብረወሰን ላሻሻለችው አትሌት ተጨማሪ የ50ሺ ብር ሽልማት ተበርክቷል።

የመጀመሪያዋ የቅድሚያ ለሴቶች የ5ኪሎ ሜትር ሩጫ ውድድር አሸናፊዋ አትሌት ቆንጅት ጥላሁን ስትሆን፤ እንደ ቲኪ ገላናና ሰንበሬ ተፈሪ ውጤታማ አትሌቶች የመጀመሪያ ውድድራቸውን ማሸነፍ የቻሉት በዚህ መድረክ እንደሆነም ይታወቃል።

በክብር እንግድነት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ክብርት አዳነች አቤቤንና የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ጨምሮ፤ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ መሥራች ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ፣ የውድድሩ አምባሳደር አትሌት መሠረት ደፋር፣ የውድድሩ የሦስት ጊዜ አሸናፊ አትሌት ሰንበሬ ተፈሪና የዓለም ቻምፒዮና የ5 እና 10ሺ ሜትር አሸናፊዋ ለተሰነበት ግዳይ መታደም ችለዋል።


## በጉምሩክ ኮሚሽን አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የተያዙና የተወረሱ የልዩ ልዩ ዕቃዎች እና ተሽከርካሪዎች ሽያጭ ማስታወቂያ ቁጥር 37/2015

አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የተተው፣ የተወረሱ እና በኮንትሮባንድ ተይዘው የሚገኙ የተለያዩ ንብረቶችን (ተሽከርካሪዎችን፣ ማሽነሪዎች፤ ሞባይሎችን፣ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን የተለያዩ የተዘጋጁ አልባሳት እና ሌሎች የተለያዩ ዕቃዎችን) ባሉበት ሁኔታ እና ቦታ በግልፅና በሃራጅ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡ ከዚህ በታች በቅፁ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ለጨረታ የሚቀርቡ ንብረቶች ዝርዝር መረጃ ተዘጋጅቶ ከህሙስ መጋቢት 21 ቀን 2015 ዓም ጀምሮ ለተጫራቾች በሚቀርብ የጨረታ ሰነድ ላይ የሚታወቅ መሆኑ እንገልጻለን፡፡

**በመሆኑም፡-**

1. በቅርንጫፍ ጽ/ቤታችን በጨረታ በቀረቡት ዕቃዎች ላይ ለመወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም በዘርፉ የፀና የንግድ ፍቃድ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የዘመኑ ግብር የከፈለ ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት የተሰጠ ማስረጃ ሰነዶች ኮፒ እና የጨረታ ማስከበሪያ ቼክ ወይም (C.P.O) ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር አያይዞ በኤንቨሎፕ ወይም በፖስታ በማሸግ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት የሚኖርበት ሲሆን ለሐራጅ ጨረታ ደግሞ ከጨረታ አንድ ቀን በፊት ይዞ ማስመዝገብ ይኖርበታል፡፡
2. የሚሸጠው ዕቃ ተሽከርካሪ ከሆነ ማንኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ በተ.ቁ. 1 የተገለፁ ቅድም ሁኔታዎቹን ማሟላት ሳያስፈልገው የጨረታ ማስከበሪያ ቼክ ወይም (C.P.O) ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር አያይዞ በኤንቨሎፕ ወይም በፖስታ በማሸግ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ በማስገባት በጨረታው ሊሳተፍ ይችላል፡፡
3. ተጫራቾች የግልጽ ጨረታውን ሰነድ ከሐሙስ መጋቢት 21 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ዘወትር በሥራ ሰዓት የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በመክፈል በቅ/ጽ/ቤቱ በመገኘት የጨረታ ሠነዱን መግዛት የሚችሉ ሲሆን የሐራጅ ጨረታውን ደግሞ በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት በነጻ ማግኘት ይችላሉ።
4. በግልፅ እና በሐራጅ በጨረታ ለመሳተፍ ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች የሰጡትን ዋጋ አምስት በመቶ (5%) ለጨረታ ማስከበሪያ ቼክ (CPO) በቅ/ጽ/ቤቱ አድራሻ ስም በባንክ አሠርተው ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ለተሽከርካሪ ሐራጅ ጨረታ እና የዕቃ ሐራጅ ጨረታ ላይ ለመሳተፍ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ እና ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች ብር 100,000.00 የጨረታ ማስከበሪያ ቼክ (CPO) ተጫራቹ ማስያዝ አለበት፡፡
6. ተጫራቾች በሚከተለው የጨረታ ቀናት (ስኬጁል) መሰረት መጫረት ይችላሉ።

| ተ.ቁ | የቅ/ጽ/ቤቱ ስም | የጨረታው አይነት | የንብረት መመልከቻ ቀን የጨረታ ሰነድ ከወሰዱ ቀን ጀምሮ | የጨረታው የመዝገያ እና የመክፈቻ ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት | ሐራጅ | እስከ 25/07/2015 | መጋቢት 26/07/2015 4:00 ሠዓት ጀምሮ ይካሄዳል |
| | | ግልፅ | እስከ 26/07/2015 | መጋቢት 27/07/2015 3:45 ተዘግቶ በዚያው ቀን 4፡00 ሠዓት ይከፈታል |

7. የጨረታው መክፈቻ ቦታ-አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የሚካሄድ ሲሆን ጨረታው ተጫራቾች / ህጋዊ ወኪሎቻቸው/ ባሉበት ወይም በታዛቢዎች ፊት ይከፈታል፡፡
8. ለጨረታው አሸናፊ ተጫራቾች ለጨረታው ዋስትና ያስያዙት (CPO) ከሚከፍሉት ዋጋ ጋር የሚታሰብላቸው ሲሆን ለተሸናፊ ተጫራቾች ደግሞ የጨረታው ውጤት ከተገለፀ በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡
9. አሸናፊ ተጫራቾች ማሸነፋቸውን ከተገለፀላቸው ቀን ጀምሮ በ5 ቀናት ውስጥ ያሸነፉበትን ገንዘብ ገቢ በማድረግ ዕቃውን ማንሣት ይኖርባቸዋል፡፡
10. ከላይ በተ/ቁ 8 በተገለፁት ቀናት ወስጥ ክፍያውን ገቢ ያላደረጉ እና ንብረቱን ተረክበው ያልወሰዱ ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት እና ለንብረቱ የከፈሉት ዋጋ ለመ/ቤቱ ገቢ ሆኖ ዕቃው በድጋሚ ለሽያጭ ይቀርባል፡፡
11. መ/ቤቱ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር፡- አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ -011 - 470 - 85- 03**

## አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት